# የፌዴራል አስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2012 አፈፃፀም የክትትል ሪፖርት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ
NATIONAL BANK OF ETHIOPIA

## የክትትል ሪፖርት

ሰኔ 2016 ዓ.ም.

## ማውጫ

ምስጋና ..... v

አህፅሮተ-ሪፖርት ..... v

ምዕራፍ አንድ ..... 1

1. ጠቅላላ መግቢያ ..... 1

1.1 መግቢያ ..... 1

1.2 ዓላማ ..... 2

1.2.1 ጠቅላላ ዓላማ ..... 2

1.2.2 ዝርዝር ዓላማ ..... 2

1.3 የክትትል ስልት ..... 2

1.3.1 የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ ..... 2

1.3.2 የናሙና አወሳሰድ ዘዴ ..... 3

1.4 የክትትሉ ወሰን ..... 4

1.5 የክትትሉ ውስንነት ..... 4

1.6 የሪፖርቱ አወቃቀር ..... 4

ምዕራፍ ሁለት ..... 6

2. መመሪያን ከማውጣት እና ከማስመዝገብ ሂደት አንፃር ..... 6

2.1 መመሪያን ስለማዉጣት ..... 6

2.2 መመሪያ ስለሚወጣበት ጊዜ ..... 7

- በሕጉ የሚጠበቀው ..... 7

2.3 የቅድመ መመሪያ አወጣጥ ሥነ-ሥርዓት ..... 7

2.3.1. መዝገብ ስለማደራጀት ..... 7

2.3.2. ማስታወቂያ ስለማዉጣት ........ 8

2.3.3. ለአስተያየት ማቅረብ ........ 9

2.3.4. የውይይት መድረክ ስለማዘጋጀት ........ 11

2.3.5. አስተያየት ስለመቀበልና ስለማካተት ........ 12

2.3.6. ለፍትህ ሚኒስቴር ለአስተያየት ስለመላክ ........ 13

2.3.7. የማብራሪያ ጽሑፍ ስለማዘጋጀት ........ 14

2.3.8. በሁለት ቋንቋ ከማዘጋጀት አንጻር ........ 16

2.4 መመሪያን ከማስመዝገብ እና በድረ-ገፅ ከመጫን አንፃር ........ 17

2.4.1. ነባር መመሪያዎችን ማስመዝገብ ........ 17

2.4.2. አዲስ መመሪያዎችን ማስመዝገብ ........ 17

2.4.3. መመሪያን ተደራሽ ከማድረግ አንፃር ........ 18

2.4.4 ሰርኩላር በተመለከተ ........ 19

ምዕራፍ ሶስት ........ 24

3. አስተዳደራዊ ውሳኔ አሰጣጥ እና ቅሬታ አፈታት ........ 24

3.1 አስተዳደራዊ ውሳኔ ከመስጠት አንፃር ........ 24

3.1.1. የአስተዳደር ውሳኔ ጥያቄ የሚቀርብበት ሁኔታ እና ይዘት ........ 25

3.1.2. ጥያቄን በመቀበል ማስረጃ መስጠት ........ 27

3.1.3. ጉዳዩን ስለመስማት ........ 27

3.1.4. የአስተዳደር ውሳኔ ይዘት ........ 28

3.1.5. በተገቢዉ ጊዜ መወሰን ........ 29

3.1.6. የአስተዳደር ውሳኔውን ለተገልጋዩ ስለመስጠት ........ 30

3.2 በአስተዳደራዊ ዉሳኔ ላይ የሚቀርብ ቅሬታን ከማየት አንፃር ........ 31

3.2.1. የቅሬታ ማስተናገጃ አካል ማቋቋም በተመለከተ ........ 31

3.2.2. ቅሬታውን ስለመመርመርና ስለመወሰን ........ 31

3.2.3. ውሳኔውን ለተገልጋዩ ስለማሳወቅ ........ 32

ምዕራፍ አራት ........ 34

4. መደምደሚያ እና ምክረ ሀሳብ ........ 34

*4.1 የመደማደሚያ ነጥቦች* ........ 34

4.2 ምክረ ሀሳብ ........ 36

የክትትል ሪፖርቱ አባሪዎች ........ 38

አባሪ 1፡- በክትትሉ የተዳሰሱ የህግ ማዕቀፍ ዝርዝር ........ 38

*አባሪ 2፡-* መመሪያ ለማውጣትና አስተዳደራዊ ውሳኔ ለመስጠት ስልጣን ሰጪ የሆኑ የሕግ ድንጋጌዎች ዝርዝር የሚያሳይ ........ 39

አባሪ 3፡- የብሄራዊ ባንክ መዋቅር ........ 70

አባሪ 5፡- ቃለመጠይቅ የተደረጉ ሰዎች ስም ዝርዝር ........ 72

አባሪ 6፦ አዋጁ ከወጣ በኋላ የወጡ መመሪዎች ዝርዝር ........ 73

አባሪ 7፦ ሳይመዘገቡ በስራ ላይ ያሉ አዲስ መመሪያዎች ዝርዝር ........ 75

አባሪ 8፡- የቃለ መጠይቅ ጥያቄዎች ........ 76

# ምስጋና

ለዚህ ክትትል ሪፖርት መሳካት አስተዋጽኦ ላደረጉ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ሀላፊዎች እና ባለሞያዎች በፍትህ ሚኒስቴር ስም ምስጋና እናቀርባለን፡፡

## አህፅሮተ-ሪፖርት

ይህ የክትትል ሪፖርት የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ አፈጻጸም የሚዳስስ ነው፡፡ እንደሚታወቀው በሀገራችን የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ጸድቆ በስራ ላይ ከዋለ አመታት ተቆጥረዋል፡፡ ይህ አዋጅ የአስተዳደር ተቋማት በሕግ በተሰጣቸው መመሪያ የማውጣት ስልጣን እና ባላቸው ከፊል የዳኝነት ስልጣን መሰረት በዕለት ተዕለት ተግባራቸው ውሳኔ በሚያስተላልፉበት ጊዜ የዘፈቀደ አሰራር እንዳይኖር እና የተገልጋዮች መብት ያለአግባብ እንዳይጣስ ለመከላከል ያለመ ነው፡፡

አስተዳደር ሥነ-ሥርአት አዋጁን አፈፃፀም የመከታተል አላማ ተቋማት መመሪያ ሲያወጡም ሆነ አስተዳደራዊ ውሳኔ ሲሰጡ አዋጁ ያስቀመጣቸውን ሂደቶች በማክበር ዜጎች ላይ የሚደርሰውን አላስፈላጊ እንግልት ለመቀነስ እና በቀጣይ ሂደቶቹን አልተከተለም ተብሎ ለሚነሳው የፍርድ ቤት ክርክር መንግስት የሚያወጣቸውን አላስፈላጊ ወጪዎች ለመቀነስ የወጡ መመሪዎችን ብቻ ሳይሆን በመውጣት በሂደት ላይ ያሉ ረቂቅ መመሪያዎችን ሂደት ጭምር በመፈተሽ የአዋጁን አተገባበር ማዳበር ነው ፡፡

ይህንን ክትትል ለማድረግ የመጀመሪያ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጮች ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡በዚህም መሰረት የተቋሙ ስልጣን እና ተግባር የሚወስኑ ህጎች ላይ የተደረገ ዳሰሳ፣መመሪያዎች እንዲሁም ሰርኩላር የሚባል ስያሜ የተሰጣቸው ነገር ግን የመመሪያ አይነት ህጋዊ ውጤት ያላቸው የህግ ሰነዶች ስለመኖራቸው ዳሰሳ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም በየደረጃ ያሉ የተቋሙ የስራ ክፍል ኃላፊዎች ጋር የተደረገ ቃለ መጠየቅ እንደ መጀመሪያ ደረጃ የመረጃ ምንጭ ተወስደዋል፡፡ አስተዳደራዊ ውሳኔ አሰጣጥ ጋር በተያያዘ የአቤቱታ ማቅረቢያ እና መቀበያ ቅጾችን፣ የመልስ መስጫ ቅጾች፣ የውሳኔ ናሙናዎችን የታዩ ሲሆን እንደ አጠቃላይ የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ማብራሪያ ሰነድ ለመረጃ ግብዓት ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ መረጃ ምንጮች መመሪያ አወጣጥን በተመለከተ የተቋሙ ድረ-ገፅ ላይ ምልከታ ማድረግ ፣ የሚመለከተው የፍትህ ሚኒስቴር ድረ-ገፅ አድራሻ ላይ ዳሰሳ ተደርጓል፡፡

በዚህም መሰረት በተቋሙ ጸድቀው በስራ ላይ ያሉ 166 መመሪያዎች ሲኖሩ ከነዚህም ውስጥ 25 የሚሆኑት አዋጁ ከወጣ በኋላ ወደ ስራ የገቡ ናቸው፡፡ ከነዚህ አዳዲስ መመሪያዎች የመመሪያ አወጣጥ ስርዓትን በተመለከተ መዝገብ ማደራጀት፣መመሪያዎችን ለባለ ድርሻ አካላት ለአስተያየት ማቅረብ፣የውይይት መድረክ ማዘጋጀት፣አስተያየት ተቀብሎ ማካተት(4)፣ለፍትህሚኒስቴርለአስተያየት መላክ፣ማብራሪያ ጽሁፍ ማዘጋጀት፣መመሪያዎችን ከማስመዝገብ ሁሉም መመሪያዎች ተመዝግበዋል እንዲሁም ተደራሽ ከማድረግ አንጻር ከተጠቀሱት 25 መመሪያዎች 15 የሚሆኑት ላይ አንዳንድ የመመሪያ አወጣጥ ስነ ስርዓት ድንጋጌዎችን ለመተግበር የተሞከረ ቢሆንም አዋጁ ከሚጥለው ግዴታ አንጻር አጥጋቢ በተሟላ ሁኔታ እያንዳንዱን የመመሪያ አወጣጥ ስነ ስርዓት ድንጋጌ አሟልቶ የተገኘ መመሪያ የለም ይህም በድክመት የተያዘ ነው ፡፡

በሌላ በኩል ማስታወቂያ ከማውጣት እና መመሪያዎችን በሁለት ቋንቋ ከማዘጋጀት አንጻር ተቋሙ ምንም ስራዎች አልተሰራበትም ይህም በድክመት የተያዘ ነው፡፡ መመሪያዎችን ተደራሽ ከማድረግ እና ድረ-ገጽ ላይ ከመጫን አንጻር ተቋሙ ድረ-ገጽ ላይ የተጫኑት ፍትህ ሚኒስቴር በሰጠው ቁጥር ሳይሆን በራሱ በተቋሙ በተሰጠው ቁጥር በመሆኑ ተገልጋይን የሚያደናግር እና ትክክለኛ ዳታ ለማግኘት የሚያስቸግር ነው ይህም በክትትሉ ግኝት በድክመት የተያዘ ነው፡፡

ባጠቃላይ ከላይ ለተነሱት መመሪያ አወጣጥ ጋር ተያይዞ አዋጁ ላይ የታዩ የአተገባበር ክፍተቶች እንደ ምክንያት በተቋሙ በኩል ያለው የስራ ጫና እና የሰው ሀይል እጥረት ተደጋግሞ የተነሳ ቢሆንም በክትትሉ መረዳት እንደተቻለው ለአዋጁ አፈጻጸም የተሰጠው ትኩረት አናሳ መሆኑ ነው፡፡

አስተዳደራዊ ውሳኔ አሰጣጥ እና ቅሬታ አፈታን በተመለከተ የአስተዳደር ሥነ-ስርዓት አዋጁ የተለያዩ ድንጋጌዎች ላይ መሰረት በማድረግ ክትትል ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት ተቋሙ ያለበት የአፈጻጸም ደረጃ ለመገምገም 38 የውሳኔ ናሙናዎች ተወስደው የታዩ ሲሆን በዚህም መሰረት የአስተዳደር ጥቂዎች እና ይዘት አንጻር ወጥ የሆነ አሰራር አለመኖሩ፣የውሳኔ አሰጣጥ ይዘት እና በተገቢው ጊዜ መስጠት ላይ በከፊል የአዋጁን ድንጋጌዎች ለመተግበር ጅማሬዎች ያሉ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል አስተዳደራዊ ጥያቄን ተቀብሎ ማስረጃ

መስጠት፣ውሳኔን ለተገልጋይ መስጠት፣የቅሬታ ሰሚ አካል ማቋቋምን በተመለከተ በተቋሙ ምንም ያልተሰራበት በመሆኑ በድክመት የተያዘ ነው፡፡

በተቋሙ በአንጻራዊ ሁኔታ አስተዳደራዊ ውሳኔ እና ቅሬታዎችን ተቀብሎ ከመስማት እና ከመመርመር አንጻር ጥሩ የሚባል አተገባበር ለማየት ተችሏል፡፡

በአስተዳደሩ አዋጁን በተገቢዉ ሁኔታ ከመፈፀም አኳያ ክፍተት ለታየባቸዉ ጉዳዮች ምክንያት ዋነኛ የሚባለው አዋጁ እያንዳንዱ ድንጋጌዎች የተካተቱበት በምክንያት መሆኑን ተረድቶ በመፈፀም ረገድ የትኩረት አለመስጠት መሆኑን መገንዘብ ይቻላል

በመጨረሻም የተቋሙ አስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ አፈጻጸም እንዲሻሻል የታዩ መልካም ተሞክሮዎች እንዲዳብሩ ክፍተቶች እንዲታረሙ የሚያስችሉ ምክረ ሀሳቦች ተሰጥተዋል፡፡

# ምዕራፍ አንድ

## 1. ጠቅላላ መግቢያ

### 1.1 መግቢያ

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 12 ስር ከተቀመጡት መሰረታዊ መርሆዎች ዉስጥ መንግስታዊ አሰራር ለሕዝብ ግልጽ በሆነ መንገድ መከናወን እንዳለበት እና ማናቸውም የመንግስት ባለሥልጣን ኃላፊነቱን ሲያጓድል ተጠያቂ ይሆናል የሚለዉ አንዱ ነዉ፡፡ ለዚህ ህገ መንግስታዊ መርህ ተግባራዊ ምላሽ ለመስጠት ከሚያስችሉት የህግ ማእቀፎች ውስጥ መጋቢት 29 ቀን 2012 ዓ/ም ጸድቆ የወጣው የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2012 አንዱ ነው፡፡ የአስተዳደር ተቋማት በሰዎች መብትና ጥቅም ላይ የሚያስከትሉትን ጣልቃ ገብነት በሕግ የሚመራ እና ለሕግ የሚገዛ መሆኑን ለማረጋገጥ እንዲሁም የአስተዳደር ተቋማት የውሳኔ አሰጣጥና የመመሪያ አወጣጥ መርሆዎችንና ሥነ- ሥርዓት አያይዞም በስተዳደራዊ ውሳኔዎችና መመሪያዎች ቅር የተሰኘ ሰው በፍርድ ቤት የሚያስመረምርበት ስርዓት በመደንገግ አስተዳደራዊ ፍትህ ማስፈን የሚያስችል ስለመሆኑ በአዋጁ መግቢያ ተገልጿል ፡፡

ፍትህ ሚኒስቴር አዋጁ ለመንግስት እና የህዝብ አስተዳደር ያለውን የላቀ ፋይዳ በመገንዘብ የአስተዳደር መስሪያ ቤቶችና የፌዴራል መንግስቱ የአስተዳደር ተቋማት የበላይ አመራሮች በስልጠና መልክ አዋጁን የማስተዋወቅ ተግባር ሲያከናውን ቆይቷል፡፡

እንዲሁም ፍትህ ሚኒስቴር ከተሰጠው ስልጣን መካከል በአዋጅ ቁጥር 943/2008 አንቀፅ 6(6) ላይ በፌደራል መንግስቱ የሚወጡ ሕጎች ወጥነት ባለው መልኩ ተግባራዊ መደረጋቸውንና አስፈፃሚ መስሪያ ቤቶችም ስራቸውን በህጉ መሰረት መስራታቸውን የመቆጣጠርና የማረጋገጥ ሀላፊነት አንዱ በመሆኑ ይህንን ስልጣን እና ተግባር ለመወጣት የፌደራል ህጎች ተፈጻሚነት መከታተያ የስራ ክፍል በዳይሬክቶሬት ደረጃ ተቋቁሞ በተመረጡ ተቋማትና ሕጎች ላይ የተለያዩ የአፈጻጸም ክትትሎችን በመስራት ሪፖርት ሲያቀርብ መቆየቱ ይታወሳል፡፡ በመሆኑም በ2016ዓ.ም ከህዳር 2016 እስከ የካቲት 2016 ዓ.ም የፌደራል የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2012 አተገባበር በኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ያለውን አፈጻጸም የሚዳስስ የክትትል ሪፖርት በዚሁ መሰረት የቀረበ ነው፡፡

## 1.2ዓላማ

### 1.2.1 ጠቅላላ ዓላማ

በኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ የመመሪያ አወጣጥ፣ አስተዳደራዊ ዉሳኔ አሰጣጥ እና ቅሬታ አፈታት ሂደት የፌዴራል አስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2012 የተከተለ ስለመሆኑ መዳሰስ ነው ።

### 1.2.2 ዝርዝር ዓላማ

- የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጁን ከመፈፀም አንፃር የሚታዩ ጥንካሬዎችንና ክፍተቶችን መለየት፣
- የታዩ ክፍተቶችን ከነ ምክንያታቸዉን በመለየት የሚታረሙበትን መንገድ መጠቆም ፣
- እንዲሁም የታዩ ጥንካሬዎች መልካም ተሞክሮ በመሆናቸው እውቅና መስጠትና እንደ አሰራር እንዲቀጥሉ ማድረግ ነው።

## 1.3 የክትትል ስልት

### 1.3.1 የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ

**ሀ/ የሕጎች ዳሰሳ**

የኢፌዲሪ መንግስት ሰራተኞች ማህበራዊ ዋስትና አስተዳደር መመሪያን ከማዉጣት እና አስተዳደራዊ ዉሳኔ ከመስጠት አንፃር ያለዉን ሥልጣን እና ተግባሩ ለመረዳት ያስችለን ዘንድ የሚከተሉት የህግ ማዕቀፎች ላይ ዳሰሳ ተደርጓል።

- የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ማቋቋሚያ / እንደተሻሻለ / አዋጅ ቁጥር 591/2000
- የባንክ ሥራ አዋጅ ቁጥር 592/2008፣
- የብሔራዊ የመድን ሥራ (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር 1163/2019፣
- አነስተኛ የፋይናንስ ሥራ አዋጅ ቁጥር 626/2009
- 1282/2015 የአነስተኛ ፋይናንስ ሥራ (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር 1164/2019
- በተንቀሳቃሽ ንብረት ላይ የሚመሰረት የዋስትና መብት አዋጅ ቁጥር 1147/2019
- የብሔራዊ የክፍያ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 718/2011
- በተቋሙ የወጡ 166 መመሪያዎች
- በተቋሙ የወጡ 18 ሰርኩላሮች

ለ/**ቃለ-መጠይቅ**

**ከአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ አፈፃፀም ጋር ተያያዘ ከመመሪያ አወጣጥ፣ አስተዳደራዊ ውሳኔ አሰጣጥ እና ቅሬታ አሰማም ጋር በተያያዘ ከሚመለከታቸዉን 9 የስራ ክፍል ኃላፊዎች እና ባለሙያዎችን ቃለ-መጠይቅ በማድረግ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡**

**ሐ/ የሰነድ ማስረጃዎች**

**የፌዴራል አስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ከመዉጣቱ በፊትም ሆነ ከወጣ በኂላ በተቋሙ የወጡ አዲስ እና ነባር መመሪያዎችን የተመለከቱ፣የአስተዳደር ውሳኔ እንዲሰጥ እና ቅሬታዎች እንዲፈቱ የሚቀርቡ አቤቱታዎች እና ምላሽ የተሰጡባቸዉን መዛግብት፣ የተቋሙን አወቃቀር የሚያሳይ ኦርጋኖ ግራም፤የዜጎች ቻርተር ፤የተቋሙ ድረ-ገፅ እና የፍትህ ሚኒስቴር ድረ-ገፅ ላይ ምልከታ ማድረግ ለክትትል ሪፖርቱ በመረጃ ምንጭነት ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡**

### 1.3.2 የናሙና አወሳሰድ ዘዴ

**ለክትትሉ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች ከጉዳዩ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ካላቸው ሰዎች ለማግኘት እንዲቻል ዓላማ-መር** (purposive sampling Technique) **የናሙና አወሳሰድ ዘዴ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ በዚህ መሰረት አጠቃላይ የተቋሙን አሰራር ሊያሳይ ይችላል በማለት መመሪያ ከማውጣት፣ አስተዳደራዊ ውሳኔ ከመስጠትና ቅሬታ ከመስማት ጋር ግንኙነት ያላቸው የስራ ክፍሎች ተመርጠው በአጠቃላይ** 9 **ኃላፊዎች እና ባለሞያዎች ጋር ቃለ-መጠየቅ በማድረግ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡**

**ለዚህ ክትትል ዓላማ-መር** (purposive sampling) **ናሙና አወሳሰድ ዘዴ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ በዚህም መሰረት ከመመሪያ አወጣጥና አስተዳደራዊ ውሳኔ አሰጣጥ ጋር በተያያዘ ቁልፍ መረጃ የሚገኝባቸውን** Bank supervision Directorate, Insurance supervision Directorate,Foreign Exchange monitoring & reserve management Directorate,Payment & Settlement Sysytems Directorate,Currency Management Directorate,Microfinance Supervision Directorate,Monetary & Financial Analysis,law directorate **ሀላፊዎች እና ባለሞያዎች ጋር ቃለ መጠይቅ ተደርጓል፡፡**

የአስተዳደር ውሳኔ ናሙና አወሳሰድ በተመለከተ ከየውሳኔዎቹ ዓይነትና ባህሪ የተቋሙን አሰራር ሊያሳይ በሚችል መልኩ የተሰጡ 38 የውሳኔ ናሙናዎች በመውሰድ ከአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ አፈጻጸም አንጻር ታይተዋል፡፡

## 1.4 የክትትሉ ወሰን

ይህ ክትትል ከጊዜ አንፃር ከህዳር እስከ ጥር ወር 2016 ዓ/ም ድረስ ባሉት ሶስት ወራት ዉስጥ የተከናወነ በመሆኑ ከእነዚህ የጊዜ ወሰን ዉጭ ያሉትን የተቋሙን አፈፃፀም የሚያካትት አይደለም፡፡ በክትትሉ የታየው  የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ አፈፃፀም ሲሆን ከዛ ውጭ ያሉ ተቋሙን ስልጣን እና ተግባር የሚመለከት አይደለም፡፡

## 1.5 የክትትሉ ውስንነት

- ተቋሙ  ክትትል በተደረገበት ጊዜ በአዳዲስ የስራ ክፍሎች እና አመራሮች  የተዋቀረ እና በአግባቡ መዋሀድ ያልተፈጠረ በመሆኑ አስፈላጊውን መረጃ ከተቋሙ በተሟላ አኳኋን ያለማግኘት ችግር ቢኖርም በቃለ መጠይቅና በውይይት የተገኘውን መረጃና በሕጎቹ ላይ የተመለከቱትን ሁኔታዎች በማሰባጠር የተሟላ መረጃ ለመያዝ ጥረት ተደርጓል፡፡
- ሁሉንም አዋጆች፣ደንቦችእና መመሪያዎች በዝርዝር ከማየት አኳያ ሙሉ በሙሉ ለመዳሰስ ቢያስቸግርም ለክትትሉ ዓላማ በቂ ነው በሚል እስከ ታሰበበት ድረስ ለመዳሰስ ተሞክሯል፡፡
- በክትትል ጊዜ የተቋሙ የስራ ክፍል ሀላፊዎች በተለያዩ ስራዎች እና ስብሰባዎች በነበረው ጫና በተፈለገው ጊዜ መረጃዎችን ለማግኘት አስቸጋሪ አድርጎታል፡፡
- ለክትትል የመጡ ባለሞያዎች ተረጋግተው ሰነዶችን ለመመርመር የሚያስችል የስራ ቦታ አለመኖር እክል ፈጥሮአል ነገር ግን የክትትል ጊዜውን በማራዘም እና የተገኘው ቦታ ላይ (ኮሪደር፣ መዝገብ ቤት ፣ የስብሰባ አዳራሾችን ) በመጠቀም ተገቢውን ማስረጃ ለመሰብሰብ ጥረት ተደርጓል፡፡

## 1.6 የሪፖርቱ አወቃቀር

ይህ ክትትል ሪፖርት በአራት ምዕራፎች የተከፋፈለ ሲሆን በመጀመሪያው ምዕራፍ መግቢያ፣ የክትትሉን አላማ፣ የመረጃ አሰባሰብ እና የናሙና አወሳሰድ ዘዴን፣ የክትትሉ ወሰን እና ውስንነቶች የተገለጸበት ነው፡፡

በሁለተኛው ምዕራፍ በፌዴራል አስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ መሠረት የአስተዳደሩ ነባር መመሪያዎች አመዘጋገብና ድረ-ገጽ ላይ መጫንን እንዲሁም ከአዋጁ መውጣት በኂላ የተዘጋጀ መመሪያን በተመለከተ የቅድመ መመሪያ አወጣጥ ሥነ-ሥርዓት አፈጻጸም በዝርዝር የተዳሰሰበት ነው፡፡

በሦስተኛው ምዕራፍ በአዋጁ የተመለከቱትን የአስተዳደር ውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶችን ከመከተል አንጻር ማለትም የአስተዳደር ውሳኔ ጥያቄ የሚቀርብበት ሁኔታ እና ይዘት፣ ጉዳዩን ስለመስማት፣ የአስተዳደር ውሳኔ ይዘት፣ በተገቢው ጊዜ ከመወሰን አንጻር እና በአስተዳደር ውሳኔ ላይ ስለሚቀርብ ቅሬታ ጋር በተያያዘ ከአዋጁ ያለው አፈጻጸም ለመቃኘት ተሞክሯል ፡፡ በመጨረሻው ምዕራፍም በክትትሉ ከተለዩ ግኝቶች በመነሳት መደምደሚያ እና ምክረ ሃሳብ ተሰጥቶበታል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# 2. መመሪያን ከማውጣት እና ከማስመዝገብ ሂደት አንፃር

## 2.1 መመሪያን ስለማዉጣት

- **በሕጉ የሚጠበቀው**

የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2013 አንቀጽ 4 መሠረት ማንኛውም የአስተዳደር ተቋም በሕግ በተሰጠው የውክልና ሥልጣን መሠረት መመሪያ ማውጣት ይችላል፡፡ የአስተዳደር ተቋም መመሪያ የሚያወጣው በአስተዳደር አዋጁ ላይ በተደነገገው ሥነ-ሥርዓት መሠረት ብቻ ነው፡፡

- **ግኝት**

የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ይክ ክትትል እስከ ተደረገበት ጊዜ ድረስ መመሪያ እንዲያወጣ በየኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ማቋቋሚያ (እንደተሻሻለ) አዋጅ ቁጥር 591/2000፣ የባንክ ሥራ አዋጅ ቁጥር 592/2008፣ የብሔራዊ የመድን ሥራ (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር 1163/2019፣ አነስተኛ የፋይናንስ ሥራ አዋጅ ቁጥር 626/2009 1282/2015 የአነስተኛ ፍይናንስ ሥራ (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር 1164/2019 በተንቀሳቃሽ ንብረት ላይ የሚመሰረት የዋስትና መብት አዋጅ ቁጥር 1147/2019 የብሔራዊ የክፍያ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 718/2011 በተሰጠው የውክልና ሥልጣን መሠረት የአዋጆቹን ማስፈፀሚያ 166 መመሪያዎች ጸድቀው በስራ ላይ ያሉ መሆናቸውን እና 18 ሰርኩላር በሚል ስያሜ የወጡ ህጋዊ ሰነዶች መኖራቸውን መገንዘብ ተችሏል ፡፡ በተጨማሪም በአዋጆቹ ላይ መመሪያ እንዲያወጣ በአስገዳጅ ሁኔታ የተቀመጡ 39 ጉዳዮች ላይ መመሪያ በማውጣት ስራ መዋላቸውን መመልከት ተችሏል ፡፡

- **በጥንካሬ የታየ**

ተቋሙ በተሰጠው ህግ የማውጣት ውክልና ስልጣን ስር ለስራው አስፈላጊ የሆነ መመሪያ አውጥቶ ስራ ላይ ያዋለ መሆኑ በጥንካሬ ተወስዷል፡፡

- **በክፍተት የታየ**

የለም፡፡

## 2.2 መመሪያ ስለሚወጣበት ጊዜ

- **በሕጉ የሚጠበቀው**

በአዋጁ አንቀጽ 5 መሰረት ማንኛዉም የአስተዳደር ተቋም ሊያወጣ የሚገባውን መመሪያ አስመልክቶ በእናት ሕጉ መመሪያ እንዲያወጣ በአስገዳጅ ሁኔታ በተደነገገ ጊዜ በሦስት ወራት ውስጥ አስገዳጅ ባልሆነ ሁኔታ በተደገገ ጊዜ ደግሞ በተገቢው ጊዜ ውስጥ መመሪያውን ማውጣት እንዳለበት ይደነግጋል ፡፡

- **ግኝት**

ከላይ በተዘረዘሩት አዋጆች መሰረት በአስገዳጅነት ሁኔታ እና በፍቅድ ስልጣን መመሪያ እንዲያወጣ ስልጣን በተሰጠዉ መሰረት በእናት ህጉ በአስገዳጅ ሁኔታ እንዲወጡ የሚጠበቁ መመሪያዎችን በማውጣት በስራ ላይ መዋላቸውን ለክትትሉ አላማ ከተሰበሰቡ ማስረጃዎች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

- **በጥንካሬ የታየ**

ተቋሙ የአዋጆችን ማስፈፀሚያ መመሪያ በተገቢው ጊዜ ውስጥ ማውጣቱ በጥንካሬ ተወስዷል፡፡

- **በክፍተት የታየ**

**የለም**

## 2.3 የቅድመ መመሪያ አወጣጥ ሥነ-ሥርዓት

የፌዴራል አስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ከወጣ በኋላ ተቋሙ የተለያዩ አዋጆች ላይ የተሰጠውን ስልጣን እና ተግባር ለማስፈጸም የሚረዱ  መመሪያዎችን አውጥቶ በሥራ ላይ ያዋለ መሆኑን ክትትሉን ለማድረግ የተሰበሰቡት መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ስለሆነም አዋጁ ከወጣ በኋላ ጸድቀው በስራ ላይ ያሉ መመሪያዎች በአዋጁ የተቀመጡ መርሆዎችን የተከተሉ ስለመሆናቸው ወይም አለመሆናቸዉ እንደሚከተለው ተዳሰዋል፡፡

### 2.3.1. መዝገብ ስለማደራጀት

- **በህጉ የሚጠበቀዉ**

በአዋጁ አንቀጽ 7 መሠረት ማንኛዉም የአስተዳደር ተቋም የሚያወጣውን መመሪያ በተመለከተ ስለመመሪያ አወጣጥ ሂደቱም ሆነ ይዘቱ የተደራጀ መረጃ ለማግኘት እንዲቻል እና ከአወጣጥ ሂደቱ ጋር ተያይዞ ለሚቀርብ ህጋዊ ተቃውሞ ማስረጃ እንዲሆን በማሰብ የተደራጀ መዝገብ እንዲኖር ይደነግጋል፡፡ መዝገቡ የመመሪያውን አወጣጥ መርሃ ግብር፣ የረቂቅ መመሪያው ዝግጅት በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ የሚያመለክት ፣ ረቂቅ መመሪያውን በተመለከተ የታተሙ ማስታወቂያዎች፣ በረቂቅ መመሪያው ላይ አስተያየት ስለሚቀርብበት ጊዜ እና ረቂቅ መመሪያውን በተመለከተ የተሰበሰቡ አስተያየቶችንና በአስተዳደር ተቋሙ በአስተያየቶቹ ላይ የተወሰዱ አቋሞችን የያዘ እንዲሆን ይጠበቃል፡፡

- **ግኝት**

የአስተዳደር ሥነ-ስርዓት አዋጁ ከወጣ በኋላ በተለያዩ የስራ ክፍሎች 40 መመሪያዎች ጸድቀው በስራ ላይ የዋሉ መሆናቸውን ክትትሉን ለማድረግ ከተሰበሰቡ መረጃዎች መረዳት ተችሏል፡፡ ከነዚህም መመሪያዎች ውስጥ የተሽከርካሪ  መድን ዋስትና ዝቅተኛ አረቦን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 60/2003፣ Directive to licensing of a takaful  operator or authorization of window takaful operator STB1/2020 ላይ ብቻ የተደራጀ መዝገብ ስለመኖሩ ለማየት ተችሏል፡፡

- **በጥንካሬ የታየ**
  **የለም**
- **በክፍተት የታየ**

መዝገብ ከማደራጀት አንጻር አዋጁ ከወጣ በኋላ የወጡ መመሪያዎች የተደራጀ መዝገብ እንዲኖራቸው ህጉ በሚያስቀምጠው መሰረት በ23 መመሪያዎች ላይ የተደራጀ መዝገብ አለመኖሩ በክፍተት የሚወሰድ ነው ፡፡ ይህም በአዋጁ ከማስፈጸም አንጻር የታየ ትልቅ ድክመት በመሆኑ ሊሻሻል የሚገባው ነው፡፡

### 2.3.2. ማስታወቂያ ስለማዉጣት

- **በሕጉ የሚጠበቀው**

በአዋጁ አንቀጽ 8 መሠረት የአስተዳደር ተቋም መመሪያ ከማውጣቱ በፊት ስለሚያወጣው ረቂቅ መመሪያ ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ እና የተቋሙን ድረ ገጽ ጨምሮ በሌሎች የመገናኛ ብዙሃን የመመሪያውን ረቂቅ ለማዘጋጀት መሰረት የሆነውን ሕጋዊ ሥልጣን እና በመመሪያው

ስለሚካተቱት ርዕሰ ጉዳዮች፣ የረቂቅ መመሪያውን ቅጂ ማግኘት የሚቻል ስለመሆኑና የሚገኝበትን ሁኔታ፣ በረቂቅ መመሪያው ላይ ሰዎች አስተያየታቸውን መቼ እና እንዴት ሊያቀርቡ እንደሚችሉ እና በዚህ አዋጅ አንቀጽ ሰባት በተመለከተው መዝገብ ላይ የሰፈሩ መረጃዎችን የትና መቼ ማግኘት እንደሚቻል የሚገልፅ መረጃ የያዘ ማስታወቂያ ማውጣት እንዳለበት ተደንግጓል፡፡

- **ግኝት**

የአስተዳደር ሥነ-ስርዓት አዋጁ ከወጣ በኋላ የወጡ 40 መመሪያዎች ላይ ማስታወቂያ ወጥቶ አያውቅም፡፡ በቃለ መጠይቅ የተገኘው ማስረጃም በተቋሙ ባለ ድርሻ አካላት በደብዳቤ እንዲያውቁት ከማድረግ ባለፈ ስራዎች እንደማይሰሩ መረዳት ተችሏል፡፡

- **በጥንካሬ የታየ**

የለም፡፡

- **በክፍተት የታየ**

በአዋጁ መሠረት ተቋሙ መመሪያዎችን ከማፅደቁና ከማስፈፀሙ በፊት በቂ በሆነ ጊዜ ዉስጥ ማስታወቂያ ማውጣት ይጠበቅበት ነበር፡፡ይሁን እንጂ ተቋሙ በሁሉም መመሪያዎች ላይ ማስታወቂያ ያላወጣ በመሆኑ በድክመትተወስዷል፡፡

### 2.3.3. ለአስተያየት ማቅረብ

- **በህጉ የሚጠበቀዉ**

ረቂቅ መመሪያን ለአስተያየት ስለመላክ በሚደነግገው የአዋጁ አንቀጽ 9 ድንጋጌ መሰረት የአስተዳደር ተቋሙ ለሕዝብ ያሳወቀውን ረቂቅ መመሪያ ለሚመለከታቸው የአስተዳደር ተቋማትና ለሌሎች ባለድርሻ አካላት ለአስተያየት መላክ አለበት፡፡ የሚመለከታቸው የአስተዳደር ተቋማትና ሌሎች ባለድርሻ አካላት በረቂቅ መመሪያው ላይ አስተያየት ካላቸው አስተያየታቸውን ተቋሙ በሚወስነው የጊዜ ገደብ ውስጥ በጽሁፍ መላክ እንዳለባቸዉ በግልፅ ተደንግጓል፡፡

- **ግኝት**

መመሪያዎችን ለባለ ድርሻ አካላት ለአስተያየት ከመላክ አንጻር በሰነድ ከታች የተዘረዘሩት ስድስት መመሪያዎች

1.የተሽከርካሪ መድን ዋስትና ዝቅተኛ አረቦን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 60/2023፣

2.Licensing and supervision of banking business management of unclaimed liabilities of a bank

3. Equity investment by foreign national of Ethiopia origin in bank /insurance companies /micro finance institution directive*ረቂቅ መመሪያ* ፣

4.Froud monitoring directive

5.Directive to licensing of a takaful operator or authorization of window takaful operator

6.Requirement for ensuring provision of suitable banking service to persons with disability

*ረቂቅ መመሪያዎች* ላይ ለባለ ድርሻ አካላት አስተያየት እንዲሰጡ ደብዳቤ የተላከ ስለመሆኑ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በእንዲሁም ተ.ቁ 6 ላይ የተጠቀሰው *መመሪያ* ከሚመለከታቸው ባለ ድርሻ አካላት በተጨማሪ የኢትዮጵያ አይነ ስውራን ማህበር እና የኢትዮጵያ አካል ጉዳተኞች ማህበር ረቂቅ መመሪያው ላይ አስተያየት እንዲሰጡበት የተላከ ስለመላኩ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በቃለ-መጠይቅ ከተገኘው ማስረጃ የህግ ክፍሉን ጨምሮ ሁሉም የስራ ክፍሎች ለባለ ድርሻ አካለት ተልኮ አስተያየት ሳይሰጥበት ወደ ስራ የሚገባ *መመሪያ* እንደሌለ ነገር ግን የሰነድ ማስረጃዎች በአግባቡ ማቅረብ አለመቻሉን ተጠቅሷል፡፡ ባለ ድርሻ አካላት አስተያየት ሊሰጡ የሚገባ ስለመሆኑም በቂ ግንዛቤ እንዳለ መረዳት ተችሏል፡፡

- **በጥንካሬ የታየ**

ረቂቅ መመሪያ ላይ አስተያየት እንዲሰጥበት ለሚመለከታቸዉ አካላት መላክን በተመለከተ በአዋጁ መሰረት ስድስት መመሪያዎች ላይ ባለ ድርሻ አካላት አስተያየት እንዲሰጡ ደብዳቤ የተላከ መሆኑን እና አንድ መመሪያ ላይ ሌሎች አካላትም አስተያየት እንዲሰጡ መደረጉ በጥንካሬ የሚወሰድ ነው፡፡

- **በክፍተት የታየ**

በክትትሉ ግኝት መሰረት ምንም እንኳን ባለ ድርሻ አካላትን ማሳተፍ ላይ የተጀመረ አሰራር እንዳለ መረዳት ቢቻልም አሰራሩ ስለመኖሩ የቀረበ የሰነድ ማስረጃ የለም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ባለ ድርሻ አካላትን ማሳተፍ እንደሚገባ በቂ ግንዛቤ ቢኖርም ሌሎች አካላትን ማሳተፍ ያልዳበረ በመሆኑ በድክመት ተወስዷል፡፡

### 2.3.4. የውይይት መድረክ ስለማዘጋጀት

- **በሕጉ የሚጠበቀው**

በአዋጁ አንቀጽ 10 መሠረት የአስተዳደር ተቋሙ በመመሪያው ረቂቅ ላይ የጽሑፍ አስተያየት መቀበያ ጊዜ ካበቃ በኋላ መመሪያው ከመፅደቁ በፊት ማንኛውም ሰው የሚሳተፍበት የውይይት መድረክ ማዘጋጀትና ግብዓት መሰብሰብ አለበት፡፡ አስተዳደር ተቋሙ በሚያዘጋጀው የውይይት መድረክ ላይ አስተያየቶችን ማስተናገድ የሚያስችል በቂ ጊዜ መመደብ አለበት ፡፡

- **ግኝት**

በተቋሙ ፀድቆ በስራ ላይ የዋሉ ሁሉም መመሪያዎች ላይ የውይይት መድረክ ለባለ ድርሻ አካላት በማዘጋጀት አስተያየተ እንዲሰጡበት የተደረገ ስለመሆኑ ከሁሉም የስራ ክፍሎች በቃለ መጠይቅ ወቅት ለመረዳት ተችሏል፡፡ ነገር ግን የተሸከርካሪ መድን ዋስትና ዝቅተኛ አረቦን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 60/2003 ውጪ ባለ ድርሻ አካላት ቀርበው ስለመወያየታቸው የተገኘ የሰነድ ማስረጃ የለም፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ለክትትሉ አላማ ከተሰበሰቡት ማስረጃዎች መረዳት እንደሚቻለው የሚወጣው መመሪያ ይመለከታቸዋል ተብለው የሚታሰቡ ባለ ድርሻ አካላትን ከማሳተፍ ውጭ ማንኛውም ሰው የሚሳተፍበት የውይይት መድረክ የማይዘጋጅ እና ግብዓትም የማይሰበሰብ ስለመሆኑ መገንዘብ ተችሏል፡፡

- **በጥንካሬ የታየ**

በተቋሙ ባለ ድርሻ አካላትን የሚያሳትፍ የዉይይት መድረክ ማዘጋጀትን እና አስተያየታቸውን መቀበል የተለመደ አሰራር መሆኑ  በጥንካሬ የሚታይ ነው።

- **በክፍተት የታየ**

በአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጁ በሚደነግገው መሰረት የውይይት  መድረክ የሚዘጋጀው ለባለ ድርሻ አካለት ብቻ ሳይሆን ማንኛውም መመሪያው ይመለከተኛል የሚሉ ለምሳሌ እንደ ሲቪክ ማህበራት እና ሌሎች መንግስታዊ እና መንግስታዊ  ያልሆኑ ተቋማት ያሉ ለህዝብ ጥቅም የሚሟገቱ አካላት እንዲሳተፉበት በማሰብ በመሆኑ ሁሉም መመሪያዎች ላይ ለውይይት ክፍት አለመሆኑ በድክመት የሚታይ ነው ። በተጨማሪም ባለ ድርሻ አካላት ስለመወያየታቸው በቃል ከተገለጸው ውጭ የተገኘ የሰነድ ማስረጃ አለመኖሩ በመመሪያው ዝግጅት ወቅት የነበሩ ሰዎች ከሀላፊነታቸው ቢነሱ መረጃ የማይገኝ መሆኑን ያሳያል። ባጠቃላይ የውይይት መድረክ ከማዘጋጀት አንጻር ከላይ በተጠቀሱት የአዋጁ አላማዎች አንጻር በድክመት የሚታይ ነው።

### 2.3.5. አስተያየት ስለመቀበልና ስለማካተት

- **በሕጉ የሚጠበቀው**

በአዋጁ አንቀጽ 12(2) እና (3) ላይ እንደተመለከተው የአስተዳደር ተቋማት መመሪያውን ከማጽደቃቸው በፊት በረቂቁ ላይ የቀረበዉን አስተያየት ከግምት ዉስጥ በማስገባት ማስተካከያ ማድረግ አለበት ወይም አስተያየቱን የማይቀበል ከሆነም፣ የማይቀበልበትን ምክንያት የሚያብራራ ጽሑፍ ማዘጋጀት አለበት።

- **ግኝት**

የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጁን መውጣት ተከትሎ ያወጣቸው 40 መመሪያዎች ላይ በረቂቁ ላይ አስተያየት እንዲሰጥበት ለባለ ድርሻ አካላት በደብዳቤ እንደሚላክ በቃለ መጠይቅ ከተሳተፉ የስራ ክፍል ሀላፊዎች መረዳት ተችሏል ። ከዚህ በተጨማሪ ባለ ድርሻ አካላት የሚሰጡትን አስተያየት ሰብስቦ በቃል እና በጽሁፍ የተሰጠው አስተያየት ያገኘውን ተቀባይነት ወይም ውድቅ መደረጉ የሚገለጽ ሲሆን ከወጡት መመሪያዎች ውስጥ አራት መመሪያዎች (የተሽከርካሪ  መድን ዋስትና ዝቅተኛ አረቦን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 60/2003፣Licensing and supervision of banking business management of unclaimed liabilities of a bank በተመለከተ የወጣ መመሪያ ፣ Requirement for ensuring provision of suitable banking service to persons with

disability በተመለከተ የወጣ መመሪያ Directive to licensing of a takaful operator or authorization of window takaful operator የወጣ መመሪያ ) ላይ የተሰጡ አስተያየቶች እና ምላሾች ተጠቃለው ለማየት ተችሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የውይይት መድረኩ ላይ የሚነሱትን አስተያየቶች እዛው ምላሽ የሚሰጥበት አሰራር መኖሩን መገንዘብ ተችሏል፡፡ ከነዚህ ከተጠቀሱት መመሪያዎች ውጭ የባለ ድርሻ አካላት ረቂቅ መመሪያው ላይ ያቀረቡትን አስተያየት ከግምት ዉስጥ በማስገባት ማስተካከያ ስለመወሰዱ ወይም አስተያየቱ ተቀባይነት ያላገኘ ከሆነም ያላገኘበትን ምክንያት አካቶ የሚያብራራ ጽሑፍ ስለመዘጋጀቱ የተገኘ ማስረጃ የለም፡፡

- **በጥንካሬ የታየ**

አስተያየት መቀበል እና ማካተትን በተመለከተ ጥቂት በስራ ላይ የዋሉ መመሪያዎች ላይ የተሰጡ አስተያየቶች ተጠቃለው መገኘታቸው የአዋጁን አላማ ከማሳካት አንጻር የሚበረታታ በመሆኑ በጥንካሬ የታየ ነው፡፡

- **በክፍተት የታየ**

ከሚመለከታቸዉ አካላት የተሰጡ አስተያየቶችን የመቀበል ልማድ ቢኖርም ከላይ ከተጠቀሱት መመሪያዎች ውጭ ተቀብሎ ማካተቱን ወይም አለማካተቱ የሚረጋገጥበት የሰነድ ማስረጃ አለመኖሩ፤እንዲሁም አስተያየቶቹ ላይ በውይይት ወቅት እዛው ምላሽ የሚሰጥበት አሰራር መኖሩ እና ማብራሪያ ጽሁፍ አለመዘጋጀቱ የፌደራል አስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጁን በመፈፀም ረገድ ክፍተት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

### 2.3.6. ለፍትህ ሚኒስቴር ለአስተያየት ስለመላክ

- **በህጉ የሚጠበቀዉ**

በአዋጁ አንቀፅ 12(4) ላይ የአስተዳደር ተቋሙ ረቂቅ መመሪያውን ከማጽደቁ በፊት ለአስተያየት ለፍትሕ ሚኒስቴር መላክ እንዳለበት ተደንግጓል፡፡ የፍትሕ ሚኒስትርም በረቂቅ መመሪያው ላይ ያለውን አስተያየት በአስራ አምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ለአስተዳደር ተቋሙ መላክ ይኖርበታል፡፡ በዚህ የጊዜ ገደብ ውስጥ አስተያየቱን ካልላከ አስተያየት እንደሌለው ተቆጥሮ መመሪያውን የማጽደቁ ሂደት ይቀጥላል ፡፡

- **ግኝት**

የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጁ በስራ ላይ ከዋለ በኋላ የወጡ 40 መመሪያዎች መካከል ለፍትህ ሚኒስቴር የተላከ መመሪያ ስለመኖሩ በቃል የህግ ክፍሉ በኩል እንደሚፈጸም ለዚ

ክትትል አላማ በቃለ መጠይቅ ወቅት ከተገለጸው ውጭ አንድ መመሪያ ላይ (የብሄራዊ ባንክ ክፍያ መፈጸሚያ ሰነድ አውጪዎችን ፍቃድ እና ይሁንታ ስለመጠየቅ ONPS/01/2020 የተሻሻለ ONPS/09/2023) ውጭ የቀረበ ማስረጃ የለም፡፡

- **በጥንካሬ የታየ**

የለም፡፡

- **በክፍተት የታየ**

ተቋሙ ካወጣቸው በርካታ መመሪያዎች ውስጥ አንድ መመሪያ ላይ ብቻ ለፍትህ ሚኒስቴር የተላከ ስለመሆኑ ማስረጃ የተገኘ ሲሆን በቃል በተገለጸው መሰረት ረቂቅ መመሪያዎች ከመጽደቃቸው በፊት ለአስተያየት ለፍትሕ ሚኒስቴር ስለመላኩ ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ በመሆኑም መመሪያዎች ከመጽደቃቸው በፊት ለፍትህ ሚኒስቴር በመመላክ አስተያየት እንዲሰጥባቸው አለመደረጉ በክፍተት የሚታይ ነው፡፡

### 2.3.7. የማብራሪያ ጽሑፍ ስለማዘጋጀት

- **በሕጉ የሚጠበቀው**

በአዋጁ አንቀጽ 14 መሠረት ማንኛውም የአስተዳደር ተቋም መመሪያ በሚያወጣበት ጊዜ መመሪያው የወጣበት የሕግ መሠረትና ዓላማ፣ በማስታወቂያው የተሰራጨው ረቂቅና የመጨረሻ ሆኖ በወጣው መመሪያ መካከል የይዘት ልዩነት ካለ የተደረጉትን ለውጦች ከነ-ምክንያቶቹ የሚገልጽ ማስታወሻ በረቂቅ መመሪያው ላይ የቀረቡ አስተያየቶችና የተወሰዱ እርምጃዎች ማጠቃለያ የያዘ የመመሪያው ማብራሪያ ማዘጋጀት አለበት፡፡ ይህም ማንኛውም የአስተዳደር ተቋም መመሪያውን ሁሉም ሰው ተገንዝቦ ለመፈጸም እንዲችል፣ ማናቸውም መመሪያው ላይ ግልጽ ያልሆነ ድንጋጌ ካለ ለመተርጎም እንዲያስችል፣ የመመሪያውን አላማ እና የሕግ መሰረት፣ ይሄም ማለት መመሪያውን ለማውጣት ስልጣን መኖሩን የሚጠቁም ድንጋጌ ብቻ ሳይሆን መመሪያው ሊያስፈጽመው የሚያልመውን ዋናው ሕግ የሚያመላክት ማብራሪያ ጽሁፍ እንዲያዘጋጅ ግዴታ የተጣለ ስለመሆኑ በአዋጁ ማብራሪያ ላይ ተጠቅሷል፡፡

- **ግኝት**

አዋጁን ተከትሎ ከወጡ መመሪያዎች ውስጥ የተሽከርካሪ መድን ዋስትና ዝቅተኛ አረቦን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 60/2003 ብቻ የማብራሪያ ፅሁፍ የተዘጋጀ መሆኑ በሰነድ ማስረጃ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም በቃለ መጠይቅ በተገኘው መረጃ መሰረት ማብራሪያ

ጽሁፍ ማዘጋጀት የተለመደ አሰራር አለመሆኑን እና መመሪያዎች ሲዘጋጁ የመመሪያው አስፈላጊነት ላይ ቅድመ ጥናት ብቻ የሚሰራ በመሆኑ አዋጁ በሚጠይቀው ልክ መመሪያው የወጣበት የሕግ መሠረትና ዓላማ፣ በማስታወቂያው የተሰራጨው ረቂቅና የመጨረሻ ሆኖ በወጣው መመሪያ መካከል የይዘት ልዩነት ካለ የተደረጉትን ለውጦች ከነ-ምክንያቶቹ የሚገልጽ ማስታወሻ እና በረቂቅ መመሪያው ላይ የቀረቡ አስተያየቶችና የተወሰዱ እርምጃዎች የያዘ አጠቃላይ የመመሪያዎቹን አደረጃጀት በዝርዝር ያስቀመጠ የማብራሪያ ፅሁፍ አልተገኘም፡፡

- **በጥንካሬ የታየ**

የለም፡፡

- **በክፍተት የታየ**

የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጁ በስራ ላይ ከዋለ በኋላ የወጡ 25 መመሪያዎች ላይ ቅድመ ጥናት በማድረግ ብቻ የመመሪያውን መውጣት አስፈላጊነት ብቻ የሚያሳይ ሲሆን በተቋሙ የሚወጡ መመሪያዎች ቴክኒካል እና ውስብብ ከመሆናቸ አንጻር የመመሪያዎች ማብራሪያ ጽሁፍ ያልተዘጋጀ መሆኑ በድክመት የሚታይ ነው፡፡

### 2.3.8. በሁለት ቋንቋ ከማዘጋጀት አንጻር

- **በህጉ የሚጠበቀው**

የአስተዳደር ሥነ-ስርዓት አዋጁ የአስተዳደር ተቋም የሚወጣ ማንኛዉም መመሪያ የሚዘጋጀው በአማርኛና በእንግሊዝኛ ቋንቋ መሆን አለበት በሚል አንቀጽ 15(1) ላይ ተድንግጓል፡፡

- **ግኝት**

አዋጁ በስራ ላይ ከዋለ በኂላ የተዘጋጁ 40 መመሪያዎች ሲሆኑ አምስት መመሪያዎች በአማርኛ ብቻ ቀሪዎቹ መመሪያዎች በእንግሊዘኛ ብቻ የተዘጋጁ መሆናቸውን በተደረገው ክትትል ለማየት ተችሏል፡፡ አጠቃላይ በተቋሙ በስራ ላይ የሆኑ እና ፍትህ ሚኒስቴር ከተመዘገቡ 166 ነባር እና አዳዲስ መመሪያዎች ውስጥ በሁለት ቋንቋ የተዘጋጀ መመሪያ አልተገኘም፡፡ በቃለ መጠይቅ ከተገኘው ማስረጃም መረዳት እንደሚቻለው በሰው ሀይል እጥረት እና የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ከሚመራበት አለም አቀፍ ስታንዳርዶች የተነሳ መመሪያዎችን በአማርኛ ለማዘጋጀት አስቸጋሪ መሆኑን እና ወደ ፊት የሚሰራበት መሆኑ ከተገለጸው ውጭ መመሪያዎች በሁለት ቋንቋ እንዲዘጋጁ የተደረገ ጥረትን የሚሳይ ማስረጃዎች አልተገኙም ፡፡

- **በጥንካሬ የታየ**

የለም፡፡

- **በክፍተት የታየ**

ተቋሙ ካለው ሰፊ መመሪያ የማውጣት ውክልና ስልጣን መሰረት እንዲሁም በስራ ላይ ያሉ መመሪያዎች ላይ ተደጋጋሚ ማሻሻያዎች የሚያደርግ ከመሆኑ አንጻር መመሪያዎችን በሁለት ቋንቋ ማዘጋጀት ላይ ትልቅ ክፍተት የታየበት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የአስተዳደር ሥነ-ስርዓት አዋጁ ጸድቆ ወደ ስራ ከገባ አራት አመት ያለፈው ሲሆን በአዋጁ ዙሪያ ስልጠናዎች ተሰጥተው ግንዛቤ ያለ መሆኑ እና  ተቋሙ መመሪያዎችን በሁለት ቋንቋ ማዘጋጀት አለመጀመሩ አዋጁን ለማስፈጸም ያለውን ተነሳሽነት ማጣት የሚያሳይ በመሆኑ በድክመት ታይቷል፡፡

## 2.4 መመሪያን ከማስመዝገብ እና በድረ-ገፅ ከመጫን አንፃር

### 2.4.1. ነባር መመሪያዎችን ማስመዝገብ

- **በህጉ የሚጠበቀው**

በአስተዳድር አዋጁ አንቀጽ 16(4) ላይ እንደተመለከተው ማንኛውም የአስተዳደር ተቋም ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት በሥራ ላይ የነበረ መመሪያን ይህ አዋጅ በወጣ ከ 90 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለፍትህ ሚኒስቴር በመላክ እንዲመዘገብ ማድረግ አለበት፡፡

- **ግኝት**

የአስተዳደር አዋጁ ከመዉጣቱ በፊት ጸድቀው በስራ ላይ የነበሩ 141 መመያዎች ለፍትህ ሚኒስቴር ተልኮ የተመዘገበ መሆኑ መመልከት ተችሏል፡፡

- **በጥንካሬ የታየ**

የአዋጁን መውጣት ተከትሎ በርካታ መመሪያዎች ለፍትህ ሚኒስቴር በመላክ መመዝገቡ በጥንካሬ የሚታይ ነው፡፡

- **በክፍተት የታየ**

የለም፡፡

### 2.4.2. አዲስ መመሪያዎችን ማስመዝገብ

- **በህጉ የሚጠበቀው**

ማንኛውም የአስተዳደር ተቋም መመሪያ እንዳወጣ ተግባራዊ ከማድረጉ በፊት መመሪያውን ከነማብራሪያው ለፍትህ ሚኒስቴር በመላክ እንዲመዘገብ ማድረግ እንዳለበት በአዋጁ አንቀጽ 16(4) ላይ ተደንግጓል፡፡

- **ግኝት**

አስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጁ በስራ ላይ ከዋለ በኋላ የወጡ 40 መመሪያዎች ለፍትህ ሚኒስቴር ተልከው ቁጥር በመያዝ የተመዘገቡ ስለመሆኑ በቃለ መጠይቅ እንዲሁም ከፍትህ ሚኒስቴር እና ከተቋሙ ድረ-ገፅ ላይ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ እንዲሁም ሳይመዘገቡ ስራ ላይ ያሉ 8 አዲስ መመሪያዎች አሉ።

- **በጥንካሬ የታየ**

ሙሉ በሙሉ ባይሆንም አዲስ መመሪያዎችን ለፍትሕ ሚኒስትር በመላክን መመዝገብ እንደ መልከም ጅምር የሚወሰድ ነው።

- **በክፍተት የታየ**

የተወሰኑ መመሪያዎችን ሳያስመዘግቡ ስራ ላይ ማዋላቸው፣

### 2.4.3. መመሪያን ተደራሽ ከማድረግ አንፃር

- በህጉ የሚጠበቀው

ማንኛውም የአስተዳደር ተቋም ያወጣውን መመሪያ አሳትሞ ለሚመለከታቸው መንግስታዊና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ማሠራጨት እና በተቋሙ ድህረ-ገጽ ላይ መጫን አለበት፡፡ እንዲሁም ማንኛውም የመመሪያውን ቅጂ ማግኘት የሚፈልግ ሰው መመሪያውን ባለበት ሁኔታ የመመልከት ወይም ወጪውን ሸፍኖ ከአስተዳደር ተቋሙ የማግኘት መብት እንዳለዉ በአዋጁ አንቀጽ 17(2) እና (3) ላይ ተደንግጓል፡፡ ቀድሞ በነበረው አሰራር የአስተዳር ተቋማት ምን ያክል መመሪያ እንዳላቸው፣በምን ጉዳይ መመሪያ እንዳወጡ እና መመሪያው ስለመሻሩ ለህዝብ ግልጽ የሚሆንበት አሰራር ባለመኖሩ አዋጁ መመሪያዎች ለህዝብ ተደራሽ ማድረግን እንደ ግዴታ ያስቀምጠዋል፡፡ ይህ የሚሆነው መመሪያውን ወደ ስራ ከመግባቱ በፊት ለፍትህ ሚኒስቴር ልኮ ከተመዘገበ በኋላ ነው፡፡ ስለሆነው ለህዝብ ተደራሽ ሚደረገው ፍትህ ሚኒስቴር መዝግቦ በሰጠው ቁጥር ይሆናል፡፡

- **ግኝት**

አስተዳደር ስነ-ስርዓት አዋጁ በስራ ላይ ከዋለ በኋላ ሁለት መመሪያዎች Licensing and authorization of payment instrument Issuer derective no.ONPS/09/2023 መመሪያው በተደጋሚ ማሻሻያ ተደርጎበታል no.ONPS/01/2020 no.ONPS/06/2022 እና Licensing, credit information and examination fees on bank directive no.85/2022) በም/ገዢው ተፈርመው ለሚመለከታቸው አካላት እንዲያስፈጽሙ የተላኩ ስለመሆናቸው በሰነድ ማስረጃ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በተደረገው ቃለ መጠይቅ መመሪያዎችን ለሚመለከታቸው አካላት መላክ የተለመደ አሰራር መሆኑ ከስራ ክፍል ሀላፊዎች በተደጋጋሚ የተነሳ እና በቂ ግንዛቤ ያለ መሆኑ መረዳት ተችሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በተለያዩ የስራ ክፍሎች ስር ተደራጅተው 177 መመሪያዎች https;nbe.gov.et ድረ-ገፅ ላይ የተጫኑ መሆናቸውን ለማየት ተችሏል ፡፡

ነገር ግን ድረ-ገጽ ላይ መመሪያዎቹ የተጫኑት ፍትህ ሚኒስቴር ተመዝግበው በያዙት ቁጥር ሳይሆን በተቋሙ በተሰጣቸው ቁጥር ነው። ይህም በመመሪያዎቹ ላይ የፍርድ ቤት ክርክር ቢነሳ ለአንድ መመሪያ ሁለት ቁጥር ሊጠቀስ ከመሆኑም በላይ ተገልጋይን ግራ የሚያጋባ ይሆናል። ከዚህ በተጨማሪ አንዳድ መመሪያ ያልሆኑ ጉዳዩች መመሪያ በሚል ቋት ስር ተካተው የሚገኙ መሆናቸው ለምሳሌ comercial credit report indicidual comercial credit report non-indicidual የሚሉ የመመሪያ ይዘት የሌላቸው ጉዳዮች፣ አንዳንድ መመሪዎች በተቋሙ በተደረገ ለውጥ መሰረት የፈረሱ ወይም በተዋሀዱ የስራ ክፍሎች ስር ተደራጅተው የሚገኙ እና አንድ መመሪያ ተደጋግሞ የተጫነ መሆኑ መረዳት ተችሏል። ይህም ትክክለኛ ዳታ ከዌብ ሳይቱ ማግኘት እንዳይቻል አድርጎታል። ባጠቃላይ በተቋሙ ድረ-ገጽ ላይ የተጫኑት መመሪያዎች በድጋሚ ማስተካከያ ተደርጎባቸው ለህዝብ ተደራሽ እንዲሆኑ ተጨማሪ ስራዎች መስራት እንዳለበት የሚሳይ ነው።

- **በጥንካሬ የታየ**

መመሪያዎች ለሚመለከታቸው አካላት የመላክ አሰራር እና ግንዛቤ ያለ መሆኑ በጥንካሬ የሚታይ ነው።

- **በክፍተት የታየ**

በድረ-ገጽ ላይ የተጫኑት መመሪያዎች ፍትህ ሚኒስቴር ተመዝግበው በያዙት ቁጥር ሳይሆን በተቋሙ በተሰጣቸው ቁጥር መሆኑ እና የተጫኑትም መመሪዎች ዳታ የተጣራ አለመሆኑ በድክመት የታየ ነው።

### 2.4.4 ሰርኩላር በተመለከተ

- በህጉ የሚጠበቀው

የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጁ አንቀጽ 2(2) መሰረት መሠረት ማንኛውም በተገልጋዮች መብትና ጥቅም ላይ ውጤት የሚያስከትል በአስተዳደር ተቋም የሚወጣ ሰነድ በተፈለገው ስም ይጠራ ለዚህ አዋጅ አላማ ሲባል መመሪያ የሚል ስያሜ ይይዛል። በመሆኑም በዚሁ አዋጅ ስር ለመመሪያ ተግባራዊ የሚደረጉ አስተዳደር ተቋም ላይ የተጣሉ ግዴታዎች ተፈጻሚ እንዲደረጉ ይጠበቃል።

- ግኝት

አጠቃላይ በተቋሙ ሰርኩላር በሚል ስያሜ የወጡ እና በስራ ላይ ያሉ 18 መመሪያዎች እንዳሉ ከተለያዩ የስራ ክፍሎች ከተሰበሰበው የሰነድ ማስረጃ እና በተቋሙ ድረ-ገጽ ላይ በተደረገው ምልከታ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ከነዚህ መመሪያዎች ውስጥ 16 የሚሆኑት የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጁ ጸድቆ ወደ ስራ ከመግባቱ በፊት የወጡ እና በስራ ላይ ያሉ ሲሆን 2 የሚሆኑት (Cash withdrawal circular issued at july 22 /2020 no. in order to clarify directive no FIS /03/2020 implemented starting from may/2020 Circular no.BSD/20/2020 issued to banks to temporarily relax from some regulatory requirement during COVID pandemic) የተባሉት አዋጁ ከወጣ በኋላ የወጡ ናቸው፡፡ በተቋሙ በተደረገው የክትትል ስራ ወቅት ሰርኩላር በሚል ስያሜ ስለሚወጡ ህጎች ያለው ግንዛቤ ላይ በተደረገው ቃለ መጠይቅ መሰረት ሰርኩላሮች የሚወጡት የወጡ መመሪያዎችን አንዳንድ ድንጋጌዎችን ግልጽ ለማድረግ እና ተፈጻሚነታቸውን ለማረጋገጥ በሚል ነው፡፡ በዚህም መሰረት ቀድመው የወጡ ሰርኩላሮች የመመሪያ ያክል ውጤት እንዳላቸው በመገንዘብ ለፍትህ ሚኒስቴር የማስመዝገብ ስራ አልተሰራም፡፡ አዳዲስ ሰርኩላሮችን በተመለከተ Cash withdrawal circular issued at july 22 /2020 no. in order to clarify directive no FIS /03/2020 implemented starting from may/2020 ሰርኩላሩ የወጣው የተጠቀሰው መመሪያ ላይ ያሉ ድንጋጌዎች (2(1)፣5(3)፣4 8 ) ላይ ማብራሪያ ለመስጠት ነው ለሁሉም ባንኮች እና ማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት በስራ ላይ መዋሉን ለማስታወቅ በም/ገዢው ተፈርሞ ደብዳቤ ተልኳል እነዚህ የተዘረዘሩትን ድንጋጌዎች ላይ የተሰጡት ትርጉሞች ባንኮቹ እና ተቋማቱ በጥብቅ እንዲከተሉ የሚጠበቅ ነው፡፡ Circular no.BSD/20/2020 issued to banks to temporarily relax from some regulatory requirement during COVID pandemic የወጣው-ሰርኩላሩ በኮቪድ ጊዜ ባንኮች የሚጠበቅባቸውን በመመመሪያ 69/2018 ላይ የተጣለባቸውን ግዴታ እንደ የአጭር ጊዜ ብድር መሰብሰብ ፣የብድር ጥያቄዎችን ማራዘም የመሳሰሉት ግዴታዎች ላይ እፎይታ የሚሰጥ ነው፡፡ ሰርኩላሩ ለሁሉም ባንኮች ግልባጭ ተደርጎ በም/ገዢው ተፈርሞ የተላለፈ ነው፡፡ ባጠቃላይ ተቋሙ ሰርኩላሮቹን አውጥቶ ወደ ስራ መግባታቸውን ለባለ ድርሻ አካላት ከማሳወቅ ውጭ በአዋጁ መሰረት ለመመሪያ የተቀመጠውን የአወጣጥ ስርዓት የተከተለ ስለመሆኑ ማስረጃዎች አልተገኙም፡፡

- በጥንካሬ የታየ

አዳዲስ የወጡ ሁለት ሰርኩላሮች ባለ ድርሻ አካላት እንዲያውቁት መደረጉ በጥንካሬ የሚታይ ነው፡፡

- በክፍተት የታየ

በአስተዳደር ሥነ-ስርዓት አዋጁ መሰረት መመሪያ ማንኛውም ሰው ላይ ግዴታ የሚጥል ወይም መብት የሚሰጥ በማለት ያስቀመጠው ድንጋጌ መሰረት የሚስከትለው ውጤት የሚፈለግ ወይም ያማይፈለግ የሚለውን የሚያካትት ስለመሆኑ ማብራሪያው ገጽ 8 ላይ ተቀምጧ፡፡ በዚህም በተቋሙ የወጡ ሰርኩላሮች የመመሪያ ያክል ውጤት ያላቸው የህግ ሰነዶች በመሆናቸው አዋጁ ከወጣ በኋላ ወደ ስራ የገቡት ምንም አይነት የቅድመ መመሪያ አወጣጥ ስዓትን የተከተሉ አለመሆናቸው እንደ ድክመት የሚወሰድ ነው፡፡

- በህጉ የሚጠበቀው

የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጁ አንቀጽ 2(2) መሰረት መሠረት ማንኛውም በተገልጋዮች መብትና ጥቅም ላይ ውጤት የሚያስከትል በአስተዳደር ተቋም የሚወጣ ሰነድ በተፈለገው ስም ይጠራ ለዚህ አዋጅ አላማ ሲባል መመሪያ የሚል ስያሜ ይይዛል፡፡ በመሆኑም በዚሁ አዋጅ ስር ለመመሪያ ተግባራዊ የሚደረጉ አስተዳደር ተቋም ላይ የተጣሉ ግዴታዎች ተፈጻሚ እንዲደረጉ ይጠበቃል፡፡

- ግኝት

አጠቃላይ በተቋሙ ሰርኩላር በሚል ስያሜ የወጡ እና በስራ ላይ ያሉ 18 መመሪያዎች እንዳሉ ከተለያዩ የስራ ክፍሎች ከተሰበሰበው የሰነድ ማስረጃ እና በተቋሙ ድረ-ገጽ ላይ በተደረገው ምልከታ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ከነዚህ መመሪያዎች ውስጥ 16 የሚሆኑት የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጁ ጸድቶ ወደ ስራ ከመግግባቱ በፊት የወጡ እና በስራ ላይ ያሉ ሲሆን 2 የሚሆኑት (Cash withdrawal circular issued at july 22 /2020 no. in order to clarify directive no FIS /03/2020 implemented starting from may/2020 Circular no.BSD/20/2020 issued to banks to temporarily relax from some regulatory requirement during COVID pandemic) የተባሉት አዋጁ ከወጣ በኋላ የወጡ ናቸው፡፡

በተቋሙ በተደረገው የክትትል ስራ ወቅት ሰርኩላር በሚል ስያሜ ስለሚወጡ ህጎች ያለው ግንዛቤ ላይ በተደረገው ቃለ መጠይቅ መሰረት ሰርኩላሮች የሚወጡት የወጡ መመሪያዎችን አንዳንድ ድንጋጌዎችን ግልጽ ለማድረግ እና ተፈጻሚነታቸውን ለማረጋገጥ በሚል ነው፡፡ በዚህም መሰረት ቀድመው የወጡ ሰርኩላሮች የመመሪያ ያክል ውጤት እንዳላቸው በመገንዘብ ለፍትህ ሚኒስቴር የማስመዝገብ ስራ አልተሰራም፡፡ አዳዲስ ሰርኩላሮችን በተመለከተ Cash withdrawal circular issued at july 22 /2020 no. in order to clarify directive no FIS /03/2020 implemented starting from may/2020 ሰርኩላሩ የወጣው የተጠቀሰው መመሪያ ላይ ያሉ ድንጋጌዎች (2(1)፣5(3)፣4 8 ) ላይ ማብራሪያ ለመስጠት ነው ለሁሉም ባንኮች እና ማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት በስራ ላይ መዋሉን ለማስታወቅ በም/ገዢው ተፈርሞ ደብዳቤ ተልኳል እነዚህ የተዘረዘሩትን ድንጋጌዎች ላይ የተሰጡት ትርጉሞች ባንኮቹ እና ተቋማቱ በጥብቅ እንዲከተሉ የሚጠበቅ ነው፡፡ Circular no.BSD/20/2020 issued to banks to temporarily relax from some regulatory requirement during COVID pandemic የወጣው-ሰርኩላሩ በኮቪድ ጊዜ ባንኮች የሚጠበቅባቸውን በመመመሪያ 69/2018 ላይ የተጣለባቸውን ግዴታ እንደ የአጭር ጊዜ ብድር መሰብሰብ ፤የብድር ጥያቄዎችን ማራዘም የመሳሰሉት ግዴታዎች ላይ እፎይታ የሚሰጥ ነው፡፡ ሰርኩላሩ ለሁሉም ባንኮች ግልባጭ ተደርጎ በም/ገዢው ተፈርሞ የተላለፈ ነው፡፡ ባጠቃላይ ተቋሙ ሰርኩላሮቹን አውጥቶ ወደ ስራ መግባታቸውን ለባለ ድርሻ አካላት ከማሳወቅ ውጭ በአዋጁ መሰረት ለመመሪያ የተቀመጠውን የአወጣጥ ስርዓት የተከተለ ስለመሆኑ ማስረጃዎች አልተገኙም፡፡

- በጥንካሬ የታየ

አዳዲስ የወጡ ሁለት ሰርኩላሮች ባለ ድርሻ አካላት እንዲያውቁት መደረጉ በጥንካሬ የሚታይ ነው፡፡

- በክፍተት የታየ

በአስተዳደር ሥነ-ስርዓት አዋጁ መሰረት መመሪያ ማንኛውም ሰው ላይ ግዴታ የሚጥል ወይም መብት የሚሰጥ በማለት ያስቀመጠው ድንጋጌ መሰረት የሚስከትለው ውጤት የሚፈለግ ወይም ያማይፈለግ የሚለውን የሚያካትት ስለመሆኑ ማብራሪያው ገጽ 8 ላይ ተቀምጧ፡፡ በዚህም በተቋሙ የወጡ ሰርኩላሮች የመመሪያ ያክል ውጤት ያላቸው የህግ ሰነዶች በመሆናቸው

አዋጁ ከወጣ በኋላ ወደ ስራ የገቡት ምንም አይነት የቅድመ መመሪያ አወጣጥ ስዓትን የተከተሉ አለመሆናቸው እንደ ድክመት የሚወሰድ ነው።

## ምዕራፍ ሶስት

## 3. አስተዳደራዊ ውሳኔ አሰጣጥ እና ቅሬታ አፈታት

### 3.1 አስተዳደራዊ ውሳኔ ከመስጠት አንፃር

የአስተዳደር ውሳኔ ማለት መመሪያ ማውጣትን ሳይጨምር የአስተዳደር ተቋም በዕለት ተዕለት ተግባሩ በሰዎች መብት ወይም ጥቅም ላይ የሚሰጠው የአስተዳደር ውሳኔ ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 2/3/ ላይ ተደንግጓል። ከዚህ ትርጉም አንፃር የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ስልጣን ሰጪ ከሆኑ አዋጆች ላይ በተሰጠዉ ስልጣን እና ተግባር መሰረት በዕለት ተዕለት ስራዉ የሚከናዉናቸዉ ሲሆኑ ከነዚህም መካከል ለምሳሌ፡-

- የባንክ ሥራ ፈቃድ  መስጠት ወይም የስራ ፈቃድ እንዲሰረዝ መወሰን፣ ፣
- ብሔራዊ ባንክ በቂ ነው ብሎ በሚያምንበት ምክንያት ማንኛውንም የባንክ ዳይሬክተር፣ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ወይም ከፍተኛ ሥራ አስፈጻሚ ከሥራ ማገድ ወይም ማሰናበት፣
- የመድን ሥራ ለመስራት  ፈቃድ መስጠት፣
- መድን ሰጪ ዳይሬክተር ፣ ዋና ሥራ አስፈጻሚ  ከሥራ ማገድ ወይም ማሰናበት፣
- መድን ሰጪው አዲስ የመድን ውሎች እንዳይዋዋል ማገድ ወይም ሊያካሂድ በሚችለው የመድን ሥራ ዓይነቶች ላይ ገደብ መጣል፣
- የመድን ሰጪውን የአክስዮን ትርፍ ድርሻ ክፍፍል ወይም መድን ሰጪው በሞግዚት አስተዳደር ሥር እንዲሆን መወሰን፣
- ለአነስተኛ የፍይናንስ ተቋም የሥራ ፈቃድ መስጠት ወይም  ፈቃዱን መሰረዝ
- አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም የተቋሙ ሥራ ወይም ተቋሙን ከሌላ ለማቀለቀል ወይም ለመሸጥ የሚቀርብ ጥያቄን መወሰን፣
- አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም የመመሥረቻ ጽሑፉን እና የመተዳደሪያ ደንቡን ማሻሻል ወይም ፈቃድ ያገኘበት ስም ለመለወጥ የሚቀርብ ጥያቄ ላይ መወሰን፣
- አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም ከተፈቀደለት አካባቢ ውጭ ለመሥራት የቀረበ ጥያቄ ላይ መወሰን፣
- አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም ወደ ባንክ ወይም ወደ ሌላ የፋይናንስ ተቋምነት ለማሻጋገር የሚቀርብ ጥያቄ ላይ መወሰን፣

• ሰዎች ስርዓትን እንዲያቋቁሙና እንዲያከናውኑ፣ እና የክፍያ መፈጸሚያ መሳሪያዎች እንዲያወጡ የቀረበ የፈቃድ ጥያቄ ላይ መወሰን፣

• ከኤሌክትሮኒክ ገንዘብ ማስተላለፍ ስርዓት ወይም እሴት አገልግሎት ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ ቅሬታዎች ላይ መወሰን፣

• ለክፍያ ሥርዓት ኦፕሬተር፣ እና ለክፍያ መፈጸሚያ ሰነድ አውጪ ፈቃድ ወይም ይሁንታ መስጠት፣

• ለባንኮችና ለሌሎች የገንዘብ ተቋማት የብድር ጥያቄ ላይ መወሰን፣

• ተቋማት ለሚያቀርቡት የውጭ ምንዛሬ ጥያቄ ላይ መወሰን የመሳሰሉ ተቋሙ አስተዳደራዊ ውሳኔዎች ከሚሰጥባቸው ጉዳዮች ውስጥ ናቸው፡፡ ከእነዚህ አበይት ተግባራት በመነሳት በተቋሙ ውስጥ አስተዳደራዊ ውሳኔ ጥያቄ የሚቀርብበት ሁኔታ እና ይዘት፤ጉዳዩ ስለሚሰማበት ሁኔታ፣የአስተዳደራዊ ዉሳኔዉ ይዘት እንዲሁም ዉሳኔዉ ለተገልጋዩ የሚሰጥበትን መንገድ ከአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጁ አኳያ ለመዳሰስ ተሞክሯል፡፡ በዚህም በክትትል ስራው ወቅት ለማሳያ የሚሆኑ ከየ ስራ ክፍሉ የተወሰዱ 38 የውሳኔ ናሙናዎች የታዩ ሲሆን ከነዚህ ማሳያዎች በመነሳት የተቋሙን አስተዳደራዊ ውሳኔ አሰጣጥ እና ቅሬታ ላይ አፈታት ተከታዩን ግኝት ማስቀመጥ ተችሏል፡፡

### 3.1.1. የአስተዳደር ውሳኔ ጥያቄ የሚቀርብበት ሁኔታ እና ይዘት

- **በህጉ የሚጠበቀው**

በአስተዳደር ሥነ-ስርዓት አዋጁ አንቀጽ 20 ላይ በግልፅ እንደተደነገገዉ አስተዳደር ውሳኔ እንዲሰጥ የሚቀርብ ጥያቄ ጉዳዩ በሚመለከተዉ ሰዉ ወይም በወኪሉ ወይም በአስተዳደር ተቋሙ አነሳሽነት ሊጀመር ይችላል፡፡ የአስተዳደር ውሳኔ ጥያቄ በጽሑፍ ሆኖ እንደሁኔታዉ በአካል፣ በተመዘገበ ፖስታ ወይም በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ሊቀርብ እንደሚችልና የአስተዳደር ተቋሙ የአስተዳደር ውሳኔ ጥያቄ የሚቀርብበትን ቅጽ ሊያዘጋጅ እንደሚችል፤ የአቤቱታዉንም ይዘት ፡-

- ቀን፣ የአቤቱታ አቅራቢው ወይም ወኪሉ ስም፣ ፊርማ እና አድራሻ፤
- አስተዳደራዊ ተግባሩን የሚፈፅመው ተቋም ስም፤
- የአቤቱታ አቅራቢው መብት ወይም ጥቅም፤
- ተቋሙ ሊፈፅመው የሚገባ አስተዳደራዊ ተግባር፤

- ተቋሙ ለሚተገብረው አስተዳደራዊ ተግባር መሰረት የሆኑ ምክንያቶች እና ተያያዥ ማስረጃዎችን መያዝ እንዳለበት በአዋጁ አንቀፅ 21 ላይ በግልፅ ተቀምጧል፡፡

  - **ግኝት**

ተቋሙ በርካታ የሆኑ አስተዳደራዊ ውሳኔ የሚሰጥባቸው ጉዳዩች እና አካላት ያሉ መሆኑን ከተደረገው ክትትል መረዳት ተችሏል፡፡ ለምሳሌ ለባንኮች፣ ለመድን ደርጅቶች፣ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ላይ የስራ ፈቃድ የቁጥጥር ስራዎችን መስራት የመሳሰሉ ተግባራት በራሱ አነሳሽነት የሚያከናዉን ሲሆን ለነዚሁ ተቋማት የስራ ፈቃድ መስጠት፣ማደስ፣የቦርድ አባላት እና ቃለ ጉባኤ ማጽደቅ ፣የብድር ጥቄዎች ላይ መወሰን የመሳሰሉት ተግባራት ጥያቄ ሲቀርብለት አስተዳደራዊ ዉሳኔ የሚሰጥ ስለመሆኑ ለማየት ተችሏል፡፡ ጥያቄዎቹ የሚቀርቡት አስተዳደሩ ባዘጋጀዉ የአቤቱታ ማቅረቢያ ቅፅ፣በፅሁፍ ወይም በኦን ላይን መጠሪያው የአንድ መስኮት ሲስተም የተባለው በተዘጋጀ ቅጽ መሰረት ባለ ጉዳዩ ወይም በወኪሉ አማካኝነት አስተዳደራዊ ጥያቄዎች ይቀርባሉ፡፡ ይህንንም በቃለ መጠይቅ፣ ከተሰበሰቡ የሰነድ ማስረጃዎች እና የተዘጋጀው ሲስተም ላይ ምልከታ በማድረግ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም የተዘጋጁ የአቤቱታ ማቅረቢያ ቅፅ እና በተገልጋዮች በፅሁፍ የሚቀርቡ አቤቱታዎች ይዘትም በአዋጁ ላይ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ያሟሉ መሆናቸው ለመመልከት ተችሏል፡፡

  - **በጥንካሬ የታየ**

አሰተዳደሩ የአስተዳደር ውሳኔ ጥያቄ የሚቀርብበት ሁኔታ እና ይዘትን በተመለከተ አዋጁን መሰረት አድርጎ እየፈፀመ በሆኑ በጥንካሬ ተወስዷል፡፡

  - **በክፍተት የታየ**

አስተዳደራዊ ጥያቄ አቀራረብ እና ይዘት ጋር በተያያዘ የታየ ክፍተት የለም፡፡

### 3.1.2. ጥያቄን በመቀበል ማስረጃ መስጠት

- **በህጉ የሚጠበቀው**

አቤቱታ የቀረበለት ተቋም አቤቱታውን በተረከበበት ጊዜ አቤቱታውን የተቀበለ መሆኑን መዝግቦ የማረጋገጫ ጽሑፍ መስጠት እንዳለበት እና የማረጋገጫ ጽሑፉ አቤቱታውን የተቀበለ መሆኑንና ከአቤቱታው ተያይዘው የቀረቡ ሰነዶችን ዝርዝር የሚያሳይ መሆን እንዳለበት በአዋጁ አንቀፅ 22 ላይ ተደንግጓል፡፡

- **ግኝት**

አስተዳደራዊ ዉሳኔ እንዲሰጥ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ለአቤቱታ አቅራቢው አቤቱታው ስለመቅረቡ የማረጋገጫ ጽሑፍ  የማይሠጥ መሆኑን በቃለ መጠይቅ ከተገኙ ማስረጃዎች መረዳት ተችሏል ፡፡ ነገር ግን በሲስተም የቀረቡ ጥያቄዎች ባለጉዳዩ ራሱ ፕሪንት አድርጎ ማስቀረት ይችላል፡፡

- **በጥንካሬ የታየ**

የለም፡፡

- **በክፍተት የታየ**

ተቋሙ የአስተዳደር ሥነ-ሰርዓቱ በሚደነግገው መሰረት አቤቱታን ከመቀበል እና ማስረጃ ከመስጠት ጋር በተያያዘ የፅሁፍ ማረጋገጫ የማይሠጥ መሆኑ በክፍተት ተወስዷል፡፡

### 3.1.3. ጉዳዩን ስለመስማት

- **በህጉ የሚጠበቀው**

ማንኛውም አስተዳደራዊ ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት ጉዳዩ በሚገባ መሰማት እንዳለበት፤ ነገር ግን ጉዳዩን መስማት ሳያስፈልግ ውሳኔ መስጠት የሚቻለው የፍሬ ነገር ክርክር ከሌለ፤ ልዩ መብት ከሆነ ወይም የአስተዳደር ተቋሙ በህግ በአማራጭ እንዲወስን ስልጣኑ ካለው፤ ወይም አስቸኳይ ድርጊት ከሆነ የመስማት ሂደት ሳያስፈልግ ውሳኔ መስጠት እንደሚቻል በአዋጁ አንቀጽ 36 ላይ ተደንግጓል፡፡

- **ግኝት**

ለክትትሉ አላማ ከተሰበሰቡት ማስረጃዎች ተቋሙ የሚቀርቡ ጥያቄዎች የሰውም የሰነድም ማስረጃም መስማት የሚያስፈልጋቸዉ መሆናቸውን መረዳት ተችሏል፡፡ የሚቀረቡ አስተዳደራዊ ጥያቄዎች የሚያስፈልጋቸው የሰነድ ማስረጃዎች በተቋሙ ጸድቀው በስራ ላይ ባሉ

መመሪያዎች በዝርዝር የተቀመጡ ሲሆን ሌሎች ተጨማሪ ማስረጃዎች በተዘጋጁ ቅጾች ላይ በተቀመጡት መሰረት አቤቱታ አቅራቢው አሟልቶ እንዲቀርብ ይጠበቃል። የቀረቡ የሰነድ ማስረጃዎች በመመርመር እንደ ጉዳዩ ክብደት በስራ ክፍል ባለሞያዎች፣ዳሬክተሮች እና ገዢዎችዎች ውሳኔ እንደሚሰጥ ለመረዳት ተችሏል። ከዚህ በተጨማሪ ግልጽ ላልሆኑ ጉዳዮች አቤቱታ አቅራቢው ቀርቦ እንዲያስረዳ እድል በመስጠት ዉሳኔ መስጠት የተለመደ አሰራር መሆኑ ማረጋገጥ ተችሏል።

- **በጥንካሬ የታዩ**

ከአስተዳደራዊ ዉሳኔ እንዲሰጥ የሚቀርቡ አቤቱታዎች ጋር የሚቀርቡ የሰነድ ማስረጃዎች በሚገባ የሚመረመሩ እና ባለጉዳዩ ቀርቦ እንዲሰማ የሚደረግ መሆኑ በጥንካሬ ተወስዷል።

- **በክፍተት የታየ**

የታየ ክፍተት የለም።

### 3.1.4. የአስተዳደር ውሳኔ ይዘት

- **በህጉ የሚጠበቀው**

ማንኛውም አስተዳደራዊ ውሳኔ በጽሑፍ ሆኖ የውሳኔ ቀንና ቁጥር ፣ የተቋሙን ስም ፣ በክርክሩ ተካፋይ የሆኑ ወገኖችን አድራሻ፤ አከራካሪ ፍሬ ነገር፤ የማስረጃዎች ትንተና፤ የፍሬ ነገር እና የሕግ ትንታኔ እና ውሳኔ መያዝ ያለበት ስለመሆኑ በአንቀጽ 40 ላይ ተደንግጓል።

- **ግኝት**

በክትትል ስራው ወቅት ውሳኔ አሰጣጥ በአብዛኛው በጽሁፍ የሚሰጥ ሲሆን አንዳንድ ውሳኔዎች በቃል የሚመለሰቡት ሁኔታዎች እንዳሉ በቃለ መጠይቅ ወቅት መረዳት ተችሏል። ከዚህ በመነሳት በሰነድ ማስረጃነት ለናሙና ከተወሰዱ መካከል አንድ ውሳኔ በቃል የተሰሠጠ መሆኑን ለማየት ተችሏል። የውሳኔ ይዘትን በተመለከተ ለናሙና ከተወሰዱት በርከት ያሉ ውሳኔዎች ውስጥ አዋጁ በሚያስቀምጠው ልክ በጽሑፍ ሆኖ የውሳኔ ቀንና ቁጥር ፣ የተቋሙን ስም ፣ በክርክሩ ተካፋይ የሆኑ ወገኖችን አድራሻ፤ አከራካሪ ፍሬ ነገር፤ የማስረጃዎች ትንተና፤ የፍሬ ነገር እና የሕግ ትንታኔ እና ውሳኔ የያዙ ቢሆንም 6 ውሳኔዎች ላይ የህግ ትንታኔ ያልተሰጠባቸው እና 6 ውሳኔዎች ደግሞ በእንግሊዘኛ ውሳኔ የተሰጠባቸው መሆኑን ለማየት ተችሏል።

- **በጥንካሬ የታየ**

አስተዳደሩ የሚሰጣቸዉ ሁሉም ዉሳኔዎች በአብዛኛዉ የአስተዳደር ዉሳኔ ይዘት መስፈርትን ያሟሉ መሆናቸዉ እንደ ጥንካሬ ታይቷል፡፡

- **በክፍተት የታየ**

ጥቂት ውሳኔዎች ላይ የሕግ ትንታኔ በዉሳኔዉ ላይ አለመካተቱ እና አስተዳደራዊ ጥያቄዎች በጽሁፍ በአማርኛ ቀርበው እያለ በእንግሊዘና ምላሽ የተሰጠባቸው መሆኑ በክፍተት ተወስዷል፡፡

### 3.1.5. በተገቢዉ ጊዜ መወሰን

- **በህጉ የሚጠበቀው**

የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጁ አስተዳደራዊ ውሳኔ አሰታት ተገማችነትትነት ለማስፈን ውሳኔ ሳይዘገይ በተገቢው ጊዜ መሰጠት እንዳለበትና በተገቢው ጊዜ ሳይሰጥ የቀረ የአስተዳደር ውሳኔ ጥያቄውን ውድቅ በማድረግ እንደተሰጠ እንደሚቆጠር በአዋጁ አንቀጽ 33 ላይ ተደንግጓል፡፡

- **ግኝት**

የአስተዳደር ውሳኔን በተገቢው ጊዜ ከመወሰን አንጻር የአስተዳደሩ እያንዳንዱ አገልግሎት በምን ያህል ጊዜ ውስጥ መጠናቀቅ እንዳለበት በ2013ዓ/ም አስተዳደሩ ባወጣዉ የዜጎች ቻርተር ሰነድ ላይ ተቀምጧል፡፡ በዚህም መሰረት የውጭ ምንዛሪ ተመን ከማሳወቅ እስከ አዲስ የስራ ፈቃድ መስጠት ድረስ ያሉ ከ5 ደቂቃ ጀምሮ 90 ቀናት የሚፈጁ የስራ መዘርዝሮች ተለይተው መቀመጣቸውን መረዳት ተችሏል፡፡ የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጁ ተገቢው ጊዜ የሚለው ለእንዳንዱ ተቋም ወስኖ ማስቀመጥ የማይቻል በመሆኑ ተቋማቱ በራሳቸው እንደየ ስራ ባህሪው በመነሳት የዜጎች ቻርተር ላይ የሚስቀምጡት የጊዜ ወሰን ገዢ ይሆናል፡፡ በመሆኑም የዜጎች ቻርተር ላይ የተቀመጠው በተቋሙ ምን ያክል ተፈጻሚ ነው የሚለውን ለማረጋገጥ በተደረገው ቃለ መጠይቅ ስራው በሚፈልገው ፍጥነት ነው እንጂ በጥብቅ የዜጎች ቻርተር ላይ የተቀመጠውን የጊዜ ገደብ የመከተል አሰራር እንደሌለ ለመረዳት ተችሏል፡፡ በአንጻሩ ውሳኔዎች ላይ በተደረገው ምልከታ መሰረት አዳዲስ የስራ ፍቃድ ለማግኘት የሚቀርቡ ጥያቄዎች በተያዘው ጊዜ ገደብ የሚሰጡ እንዳሉ ሁሉ ከተቀመጠው የጊዜ ገደብ በላይ እንደሚወስዱ ለመረዳት ተችሏል፡፡ ከተቋሙ አመራሮች ጋር በነበረው ቃለ መጠይቅ በዜጎች ቻርተር ላይ የተቀመጠውን አገልግሎት መስጫ ጊዜ ላለመከተላቸው እንደ ምክንያት የተነሳው ከፍተኛ የሆነ የሰው ሀይል እጥት መኖሩ እና አገልግሎት ጠያቂዎች በተለያዩ ህጎች ላይ የተቀመጡ

መስፈርቶችን አሟልቶ ባለመቅረብ መመላለሶች በመፈጠራቸው መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ከላይ እንደ ምክንያት የተነሱትን ችግሮች ለመፍታት  ቻርተሩ እየተከለሰ መሆኑ ተጠቅሷል፡፡

- **በጥንካሬ የታየ**

በርካታ ውሳኔዎች በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ መወሰናቸው እና ቻርተሩ ያስቀመጠው ጊዜ ለመከተል በምክንያት የተነሱ ጉዳዮችን ግምት ውስጥ በማስገባት ለመከለስ ሂደት ላይ መሆኑ በጥንካሬ ታይቷል፡፡

- **በክፍተት የታየ**

ዉሳኔዎች ለመስጠት መዘግየት ምክንያት ቢኖርም በዜጎች ቻርተር በተቀመጠዉ የጊዜ ገደብ አለመከወናቸዉ በክፍተት ታይቷል፡፡

### 3.1.6. የአስተዳደር ውሳኔውን ለተገልጋዩ ስለመስጠት

- **በህጉ የሚጠበቀው**

የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጁ የተገልጋይን መብት ከማስከበር እና መልካም አስተዳደር ከማስፈን አንፃር ያለው ፋይዳ ከፍተኛ ስለሆነ የአስተዳደር ውሳኔውን ለተገልጋዩ መስጠት ተቋማት ላይ የተጣለ ሀላፊነት ነው፡፡ በዚህም መሰረት ማንኛውንም የአስተዳደር ውሳኔ ተገልጋዩ በጽሁፍ ይሰጠን በማለት ጥያቄ አቀረበም አላቀረበም ውሳኔው መተላለፉን በጽሁፍ ከነምክንያቱ ለተገልጋዩ መሠጠት እንዳለበ የአዋጁ አንቀጽ 39 ላይ ተደንግጓል፡፡

- ግኝት

በተቋሙ በነበረው የክትትል ቆይታ በቃለ መጠይቅ፣በሰነድ እና ሲስተም ላይ በተደረገ ምልከታ መሰረት አስተዳደራዊ ውሳኔን በጽሁፍ ውሳኔውን ከነምክንያቱ ለተገልጋዩ ከመስጠት አንጻር ወጥ የሆነ አሰራር አለመኖሩን መረዳት ተችሏል፡፡ እንዲሁም ውሳኔው የሚሰጠው ተገልጋዩ ሲጠይቅ እንጂ ልክ ውሳኔ እንዳገኘ የሚሰጥበት የአስራር ልምድ እንደሌለ ለመረዳት ተችሏል፡፡ ሌላ በኩል በሲስተም መሰረት ለቀረቡ ጥያቄዎች ጥያቄው የደረሰበትን ሂደት ጨምሮ ውሳኔ እስከተሰጠበት ጊዜ ድረስ ያለውን ሂደት ጠብቆ በተሟላ ሁኔታ እንደሚጫን እና ተገልጋይ ወደ ወረቀት በመገልበጥ መውሰድ የሚችልበት አሰራ መዘርጋቱን ለመመልከት ተችሏል፡፡

- **በጥንካሬ የታየ**

የአስተዳደር ውሳኔውን በሲስተም ላይ ባለው አሰራር በተሟላ ሁኔታ ለተገልጋይ ተዘጋጅቶ የተቀመጠ በመሆኑ በጥንካሬ የሚታይ ነዉ፡፡

- **በክፍተት የታየ**

ተቋሙ አዋጁ ባስቀመጠው መሰረት ወጥ በሆነ ሁኔታ ውሳኔዎች ከነ ምክንያታቸው ለተገልጋይ የማይሰጥ መሆኑ በድክመት ታይቷል፡፡

## 3.2 በአስተዳደራዊ ዉሳኔ ላይ የሚቀርብ ቅሬታን ከማየት አንፃር

### 3.2.1. የቅሬታ ማስተናገጃ አካል ማቋቋም በተመለከተ

- **በህጉ የሚጠበቀው**

ማንኛውም ሰዉ በተላለፈበት የአስተዳደር ውሳኔ ላይ ለአስተዳደር ተቋሙ ቅሬታ የማቅረብ መብት እንዳለዉ እና የአስተዳደር ተቋሙም የቅሬታ ማስተናገጃ አካል ማቋቋም እና ይህንኑ ለተገልጋዮች ይፋ ማድረግ እንዳለበት በአዋጁ አንቀጽ 43 እና 44 ላይ ተደንግጓል፡፡

- **ግኝት**

ተቋሙ የቅሬታ ማስተናገጃ አካል የለውም፡፡ አንድ ተገልጋይ በተሰጠው አገልግሎት ቅር ከተሰኘ እንደ አማራጭ የተቀመጠው አሰራ ወደ በላይ ሀላፊ አቤቱታውን ይዞ መሄድ እንደሆነ በክትትሉ የተሰበሰቡ ማስረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በቃለ መጠይቅ ወቅት ከተሳተፉ አመራሮች ቅሬታ ማቅረቢያ አካል ማቋቋም ተገቢ መሆኑ ታምኖበት በሂደት ላይ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

- **በጥንካሬ የታየ**

የለም፡፡

- **በክፍተት የታየ**

የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጁ ከወጣ አመታት የተቆጠሩ ቢሆንም በሙከራ ደረጃ እንኳን ያለ ቅሬታ ሰሚ አካል አለመቋቋሙ በክፍተት የሚወሰድ ነው

### 3.2.2. ቅሬታውን ስለመመርመርና ስለመወሰን

- **በህጉ የሚጠበቀው**

በአዋጁ አንቀጽ 46 መሰረት የአስተዳደር ተቋሙ የቅሬታ ማስተናገጃ አካል ቅሬታውን በሚገባ መመርመር እና የዉሳኔ ሀሳብ ለአስተዳደር ተቋሙ የበላይ ኃላፊ ወይም እሱ ለወከለዉ የሥራ ኃላፊ ማቅረብ አለበት፡፡ የአስተዳደር ተቋሙ የበላይ ኃላፊ ወይም እሱ የወከለዉ የሥራ ኃላፊ

በቅሬታ ማስተናገጃ አካል የቀረበለትን የውሳኔ ሀሳብ ተመልክቶ የሰጠው ውሳኔ የተቋሙ የመጨረሻ ውሳኔ ይሆናል፡፡

- **ግኝት**

ተቋሙ ቅሬታ ሰሚ አካል ያላቋቋመ በመሆኑ ቅሬታ ወጥ በሆነ ሁኔታ እንደማይቀርብ በክትትሉ ለማየት ተችሏል፡፡ ይኸም ባለ ጉዳዩ ቅሬታውን ይዞ ወደ ስራ ክፍል ሀላፊዎች(ዳይሬክተሮች እና ም/ዳይሬክተሮች) ይወስደዋል ወይም ቀጥታ ለገዢው ወይም ለዘርፉ ም/ገዢ በማቅረብ የተወሰኑ ውሳኔዎች ላይ ቅሬታ የሚያቀርብበት አሰራር መኖሩን ለመረዳት ተችሏል፡፡ ቅሬታዎች ሲቀርቡ ለሚመለከተው የስራ ክፍል ተመርቶ የስራ ክፍሉ ጉዳዩን በመመርመር ለበላይ ሀላፊ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፡፡ ይህም እንደየቅሬታው አይነት ተለይቶ በስልጣን ተዋረድ መሰረት ምላሽ የሚሰጥበት መሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡ ባጠቃላይ ቅሬታዎች ለተለያየ ሀላፊ ይቅረብ እንጂ በተቋሙ የመጨረሻ ውሳኔ የሚሰጠው በገዢው መሆኑን ከሁሉም የስራ ክፍሎች ሀላፊዎች ጋር በተደረገው ቃለ መጠይቅ ተረጋግጧል፡፡

- **በጥንካሬ የታየ**

የመጨረሻ ውሳኔ ሀሳብ በገዢው የሚሰጥ መሆነ እና ባለ ጉዳዩ ከባለሞያ ጀምሮ የተሰጡ ውሳኔዎችን ይዞ በየደረጃው ቅሬታውን የማቅረብ እድል የሚሰጥ አሰራ መኖሩ በጥንካሬ ተወስዷል፡፡

- **በክፍተት የታየ**

ወጥ የሆነ ቅሬታ አቀራረብ አለመኖሩ በክፍተት ተወስዷል፡፡

### 3.2.3. ውሳኔውን ለተገልጋዩ ስለማሳወቅ

- **በህጉ የሚጠበቀዉ**

የአስተዳደር ተቋሙ የተሰጠውን ውሳኔ ወዲያውኑ ለቅሬታ አቅራቢው በጽሑፍ መስጠት እንዳለበት በአዋጁ አንቀጽ 47 ላይ ተመልክቷል፡፡በዚህም መሰረት አንድ የአስተዳደር ተቋም የአስተዳደራዊ ውሳኔ በጽሁፍ መስጠት እንዳለበት ሁሉ ቅሬታው ላይ የሚሰጠውን ውሳኔ ለቅሬታ አቅራቢው በጽሁፍ እንዲሰጥ ግዴታ የሚጥል ድንጋጌ ነው፡፡

- **ግኝት**

ተቋሙ የሚቀርቡ ቅሬታዎች በተለያየ አካል የሚሰጡ በመሆናቸው እና ወጥነት የሌለው በመሆኑ ለቀረበው ቅሬታ ወዲያውኑ ውሳኔ ስለመሰጠቱ ማረጋገጫ የለም፡፡ ለምሳሌ ቃለ-ጉባኤ እንዲጸድቅ ጥያቄ ያቀረበ አንድ የግል ባንክ ቃለ-ጉባኤው እንደማይጸድቅ ከተወሰነ በኋላ ቅሬታውን ለማቅረብ በቀጥታ የሚሄድበት የቅሬታ ሰሚ አካል ባለመኖሩ ለም/ገዢ አቅርቦ ወደ ባለሞያ ተመርቶ ባለሞያው የውሳኔ ሀሳቡን መርምሮ ወዲያው ባለ ጉዳዩ የሚያውቅበት እድል ጠባብ ነው ፡፡ከዚህ በተጨማሪ ቅሬታው ላይ የሚሰጠው ውሳኔ በጽሁፍ ይሁን እንጂ ባለ ጉዳዩ ራሱ ተከታሎ ካልወሰደ በስተቀር ተቋሙ የተወሰነውን ውሳኔ መውሰድ የሚችልበት አሰራር አለመኖሮ ለመረዳት ተችሏል፡፡

- **በጥንካሬ የታየ**

የለም

- **በክፍተት የታየ**

ቅሬታ አቅራቢው ባቀረበው ቅሬታ ላይ የተወሰነውን ውሳኔ በተቋሙ ተነሳሽነት በጽሁፍ የሚደርሰው ሳይሆን ጥያቄ ሲቀርብ ብቻ በመሆኑ እንደ ድክመት ተወስዷል፡፡

## ምዕራፍ አራት

## 4. መደምደሚያ እና ምክረ ሀሳብ

### 4.1 የመደማደሚያ ነጥቦች

በኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ በተደረገው የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2012 አፈጻጸም በተደረገው ክትትል መሰረት የተስተዋሉ ክፍተቶች ተለይተው ለእነዚህ ክፍተቶች መነሻ ምክንያት የሆኑት ተለይተው በቀጣይ ማስተካከያ እንዲደረግባቸው ለማስቻል በክትትሉ የተገኙ መረጃዎች እንደሚከተለው ተጠቃለው ቀርበዋል፡-

**መመሪያን በተመለከተ፡-**

- የመመሪያዎች አወጣጥና ምዝገባ ሥርዓት ጋር በተያያዘ ተቋሙ የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጁ ከወጣ በኋላ የተቀመጡ 13 የስነ ስርዓት ድንጋጌዎች አተገባበር በክትትሉ በዋናነት የመዘነ ሲሆን አጠቃላይ አፈጻጸሙ ሲታይ ዝቅተኛ በሚባል ደረጃ ላይ እና አዋጁን በአግባቡ ከመተግበር አንጻር በሁሉም ድንጋጌዎች ስር ክፍተት የሚታይበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡
- መዝገብ ማደራጀት፣መመሪያዎችን ለባለ ድርሻ አካላት ለአስተያየት ማቅረብ፣የውይይት መድረክ ማዘጋጀት፣አስተያየት ተቀብሎ ማካተት፣ለፍትህ ሚኒስቴር ለአስተያየት መላክ፣ማብራሪያ ጽሁፍ ማዘጋጀት፣መመሪያዎችን ከማስገብእና ተደራሽ ከማድረግ አንጻር ጥቂት መመሪያዎች ላይ ለመተግበር የተሞከረ ቢሆንም አዋጁ ከሚጥለው ግዴታ አንጻር አጥጋቢ የሚባል አይደለም፡፡
- በሌላ በኩል ማስታወቂያ ከማውጣት እና መመሪያዎችን በሁለት ቋንቋ ከማዘጋጀት አንጻር በተቋሙ ምንም ስራዎች ያልተሰራበት ነው፡፡
- መመሪያዎችን ተደራሽ ከማድረግ እና ድረ-ገጽ ላይ ከመጫን አንጻር ተቋሙ ድረ-ገጽ ላይ የተጫኑት ፍትህ ሚኒስቴር በሰጠው ቁጥር ሳይሆን በራሱ በተቋሙ በተሰጠው ቁጥር በመሆኑ ተገልጋይን የሚያደናግር እና ትክክለኛ ዳታ ለማግኘት የሚያስቸግር ነው፡፡
- ሰርኩላሮችን በተመለከተ የመመሪያ ያክል ውጤት እንዳላቸው በመገንዘብ ነባር የሆኑትን አለማስመዝገብ እና አዳዲሶቹ ላይ አዋጁ በሚደነግገው መሰረት የመመሪያ አወጣጥ ስርዓቶችን ተቋሙ ያልተገበረ መሆኑ ታይቷል፡፡

- ባጠቃላይ ከላይ ለተነሱት አዋጁ ላይ የታዩ የአተገባበር ክፍተቶች በተቋሙ በኩል ያለው የስራ ጫና እና የሰው ሀይል እጥረት ተደጋግሞ የተነሳ ቢሆንም ከክትትሉ ግኝቶች መረዳት እንደተቻለው ለአዋጁ አፈጻጸም የተሰጠው ትኩረት አናሳ መሆኑ መገንዘብ ተችሏል፡፡

**የአስተዳደራዊ ውሳኔ አሰጣጥ እና ቅሬታ አፈታት**

- አስተዳደራዊ ውሳኔ አሰጣጥ እና ቅሬታ አፈታን በተመለከተ የአስተዳደር ሥነ-ስርዓት አዋጁ የተለያዩ 9 ድንጋዎች ላይ መሰረት በማድረግ ክትትል ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት ተቋሙ ያለበት የአፈጻጸም ደረጃ ለመገምገም 38 ናሙናዎች ተወስደው የታዩ ሲሆን በዚህም መሰረት የአስተዳደር ጥቄዎች እና ይዘት አንጻር ወጥ የሆነ አሰራር አለመኖሩ፣የውሳኔ አሰጣጥ ይዘት እና በተገቢው ጊዜ መስጠት ላይ በከፊል የአዋጁን ድንጋጌዎች ለመተግበር ጅማሬዎች ያሉ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡
- በሌላ በኩል አስተዳደራዊ ጥያቄን ተቀብሎ ማስረጃ መስጠት፣ውሳኔን ለተገልጋይ መስጠት፣የቅሬታ ሰሚ አካል ማቋቋምን በተመለከተ በተቋሙ ምንም የአተገባበር ጅማሮ ያልታየበት ነው፡፡
- በተቋሙ በአንጻራዊ ሁኔታ አስተዳደራዊ ውሳኔ እና ቅሬታዎችን ተቀብሎ ከመስማት እና ከመመርመር አንጻር ጥሩ የሚባል አተገባበር ለማየት ተችሏል፡፡

በአስተዳደሩ አዋጁን በተገቢዉ ሁኔታ ከመፈፀም አኳያ ክፍተት ለታየባቸዉ ጉዳዮች ምክንያት ዋነኛ የሚባለው አዋጁ እያንዳንዱ ድንጋጌዎች የተካተቱት በምክንያት መሆኑን ተረድቶ ከመፈፀም ረገድ ትኩረት አለመስጠት መሆኑን መገንዘብ ተችሏል ፡፡

## 4.2 ምክረ ሀሳብ

በክትትሉ ወቅት አዋጁን ከመፈፀም አንፃር በመሰረታዊነት የተለዩ ክፍተቶችን ለማረም እንዲችል ለተቋሙ የሚከተለዉ ምክረ ሀሳብ ቀርቧል፡፡

- በአጠቃላይ ከመመሪያ፣አስተዳደራዊ ውሳኔ አሰጣጥ እና ቅሬታ አፈታት ጋር በተያያዘ ለታዩ ክፍተቶች መንስኤ ተደርገው በስራ ክፍል ሀላፊዎች በዋናነት የተነሳው የሰው ሀይል እጥረት ተቋሙ በክትትሉ ግኝት መሰረት ያሳየውን ዝቅተኛ አፈጻጸም ግምት ውስጥ በማስገባት አፋጣኝ ምላሽ ቢሰጥበት፤
- የአስተዳደር ጥቂዎች እና ይዘት አንጻር ወጥ የሆነ አሰራር አለመኖሩ፣የውሳኔ አሰጣጥ ይዘት እና በተገቢው ጊዜ መስጠት ላይ በከፊል የአዋጁን ድንጋጌዎች ለመተግበር የታዩት ጅማሬዎች ሙሉ በሙሉ ተፈጻሚነታቸው ቢረጋገጥ፤
- በሌላ በኩል ማስታወቂያ ከማውጣት እና መመሪያዎችን በሁለት ቋንቋ ከማዘጋጀት አንጻር ተቋሙ ምንም ስራዎች ያልሰራ በመሆኑ አዋጁ ድንጋጌዎቹን ያስገባበትን ቁልፍ አላማ በመረዳት ተፈጻሚ ቢደረጉ ፤
- መመሪያዎችን ተደራሽ ከማድረግ እና ድረ-ገጽ ላይ ከመጫን አንጻር ተቋሙ ድረ-ገጽ ላይ የተጫኑት ፍትህ ሚኒስቴር በሰጠው ቁጥር ሳይሆን በራሱ በተቋሙ በተሰጠው ቁጥር በመሆኑ ተገልጋይን የሚያደናግር እና ትክክለኛ ዳታ ለማግኘት የሚያስቸግር በመሆኑ በድጋሚ ተስተካክሎ ለህዝብ ተደራሽ የሚሆንበት ስራ ቢሰራ፤
- ሰርኩላር የመመሪያ ያክል ህጋዊ ውጤት ያለው የህግ ሰነድ መሆኑን በመገንዘብ አዋጁ በሚያስቀምጣቸውን ግዴታዎች መሰረት ተፈጻሚ ቢደረግ፣
